ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 13 ሐምሌ 30/2015 ዓ.ም

የሀምሌ ወር የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ልዩ እትም



## ከህብረተሰቡ በቀረቡ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎች ላይ በተደረገ ማጣራት ከ36 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ ተደርጓል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል በከተማ እና በገጠር በህገ ወጥ መንገድ ወደ ግለሰቦች ዞሮ የነበረ 109.8 ሄክታር መሬት ወደ መሬት ባንክ ገቢ ተደርጓል ተብሏል። ይህ የተባለው የክልሉን የ2015 ዓ.ም አፈፃፀም ሪፖርት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ ለምክር ቤቱ ባቀረቡት ወቅት ነው።

ከህብረተሰቡ ... ወደ ገጽ 3 የዞረ

## ቬትናም በኮቪድ ወቅት ወደ አገራቸው ከሚመለሱ ዜጎች ከፍተኛ ጉቦ የጠየቁ ባለስልጣናት አሰረች

ገጽ 3

## የታማኝነት ሽልማት ፕሮግራም ተካሄደ

ገጽ 4

# 6ኛው ዙር ዓመታዊ የአፍሪካ አገሮች የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጉባዔ በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ ተካሄደ

6ኛው ዙር ዓመታዊ የአፍሪካ አገሮች የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጉባኤ "Promote citizen engagement in the fight against corruption and illicit financial flows, guarantee of the holistic development of the African continent" በሚል መሪ ቃል በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ ከሃምሌ 24-25 /2015 ዓ.ም ተካሂዷል።

ጉባዔው የህገ-ወጥ ገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የቴክኖሎጂ አስፈላጊነት፣ በፀረ ሙስና ትግሉ የሲቪል ማህበረሰብ ሚና እና በሌሎች ጉዳዮች ላይም መክሯል። ለሁለት ቀናት በተካሄደው ጉባዔ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶን ጨምሮ ከ40 በላይ የአፍሪካ ሀገራት የፀረ-ሙስና ተቋማት ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።



# ሀገራዊ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የጋራ ትስስር ጉባኤ ተካሄደ

የፌደራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነሮች እና በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና አባላት እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ሀገራዊ የ2015 በጀት ዓመት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የውይይት መድረክ በአዳማ ከተማ ኃይሌ ሪዞርት ተካሂዷል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ወዶ አጦ ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሀገራችንን ብልፅግና የሚያደናቅፍ እና ሰላማችንን የሚያደፈርስ አደገኛ ወንጀል በመሆኑ ሁላችንም በጋራ ልንታገለው ይገባል ብለዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ ሀገራት ይህን ለዕደገት እንቅፋት የሆነውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመቀነስ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባቸው ገልፀዋል። በ2015 በጀት ዓመት በመንግስት ተቋማት እና በልማት ድርጅቶች እንዲሁም በህዝባዊ ተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ሥራዎች እንዲሁም ሀብት የመመዝገብና የማረጋገጥ እና በ25 ዘርፎች የሙስና ስጋት ጥናት ስራ መከናወኑን አብራርተዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ አዝመራ አንዶሞ በበኩላቸው ሀገራችን ኢትዮጵያ የጀመረችውን የብልፅግና ጉዞ ዳር ለማድረስ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ላይ ትኩረት አድርገን በቅንጅት ልንሰራ ይገባል ብለዋል። በሀገር ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በማቋቋም በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ገልፀው







በቀጣይም የፌደራል እና የክልል እንዲሁም የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አሰራራቸውን በማዘመን የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ስራን በጋራ ማከናወን እንዳለባቸው መልክት አስተላልፈዋል።

በመድረኩ ለጋዜጠኞች መግለጫ የሰጡት ክቡር ም/ኮሚሽነርሥወዶ አጦ ሙስናን ለመከላከል በትውልድ ስነምግባር ግንባታ ላይ በየደረጃው በትኩረት የተሰራበት ዓመት ነበር ብለዋል። ከሥነምግባር ግንባታ ጎን ለጎን በሙስና መከላከል ላይ የተጀመረውን ትግል ውጤታማ ለማድረግ ሙስና የህብረተሰቡ አጀንዳ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ተስፋ ሰጪ ስራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል። በበጀት ዓመቱ 25 ዘርፎች ተለይተው ሙስና ያለበት ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

ሀገራዊ የሥነምግባር ... ወደ ገጽ 2 የዞረ







# የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የጤና ዐውደ ርዕይን ጎበኙ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በጤና ሚኒስቴር አማካኝነት የተዘጋጀውን የሳይንስ ሙዚየም የጤና ዐውደ ርዕይ ጎብኝተዋል። በጉብኝታቸው በጤናው ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ የለውጥ ስራዎች በተለይም በዘርፉ የሀገር በቀል እውቀቶችን ከመጠቀም እና ከማዘመን አንጻር፣ የዲጂታል ጤና ቴክኖሎጂ እንዲሁም በገጠር እና በከተማ የጤና አገልግሎትን በማዘመን ለዜጎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ እንዲሆኑ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ማየት ችለዋል።






በተጨማሪም በዘርፉ ከተደራሽነት አንጻር ወደፊት የታሰቡ አሰራሮችን የጎበኙ ሲሆን፤ ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ በሚሰሩ ጉዳዮች ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ መያዝ ተችሏል። ከጉብኝቱ ጎን ለጎን የደም ልገሳ ያካሄዱ የኮሚሽኑ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እያደረገ ያለውን በጎ እንቅስቃሴ አጠናክሮ እንዲቀጥል አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። በጉብኝቱ ማጠቃለያ አስተያየታቸውን የሰጡት የሥነምግባር ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር ወዶ አጦ ሀገራችን በርካታ እምቅ አቅም ያላት በመሆኑ በየዘርፉ ተጠናክሮ መስራት ከተቻለ በፍጥነት መልማት እንደሚቻል ገልጸዋል። አክለውም በመድኃኒት አቅርቦትና ግዥ የሚስተዋሉ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎች እና ብልሹ አሰራሮችን በጋራ በመታገል ረገድ ከተቋሙ ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።

# በ2015 በጀት ዓመት ያለአግባብ ሊመዘበር የነበረን ግምቱ 7,257,269.08 ብር እና 56,900 ካሬ ሜትር የህዝብና የመንግስት ሀብት ማትረፍ እንደተቻለ ተገለፀ።

በአብክመ የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በ2015 በጀት አመት በክልሉ ውስጥ ያለአግባብ ከመመሪያ እና ከአሰራር ውጭ ከተለያዩ ተቋማት ላይ ሊመዘበር እና ሊጭበረበር የነበረን የህዝብና የመንግስት ሀብት ማዳን መቻሉን ኮሚሽኑ በሪፖርቱ አሳውቋል።

እንደሪፖርቱ ዘገባ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በክልሉ ከተለያዩ ተቋማት ላይ ህግና መመሪያን ያልተከተሉ ብልሹ አሰራሮች አሉ የሚሉ ጠቅላላ 573 ጥቆማዎች ከህብረተሰቡ እንደተሰጠ ተገልጿል። ከተሰጡት ጥቆማዎች ውስጥ 58 ጥቆማዎች በኮሚሽኑ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ የተፈቱ፣ 226 ጥቆማዎች ተጨማሪ ምርመራ እንዲካሄድባቸው ለፖሊስ ኮሚሽን የተላኩ፣ 251 ጥቆማዎች በአስተዳደራዊ እርምጃ የተፈቱ እና 38 ጥቆማዎች ደግሞ በሂደት ላይ ያሉ መሆኑንም የኮሚሽኑ ሪፖርት ገልጿል።




ይህ በእንዲህ እንዳለ በክልሉ ውስጥ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የቀረቡ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት እና ክትትል በማድረግ ያለአግባብ ከመመሪያ እና ከአሰራር ውጭ ሊመዘበር የነበረው የህዝብና የመንግስት ሀብት ግምቱ 7,257,269.08 ብር የሆነ እና 56,900 ካሬ ሜትር የከተማና የገጠር መሬት ከዘራፊዎች ማትረፍ እንደተቻለ ተገለጿል።

በተጨማሪም ከመመሪያ እና ከአሰራር ውጭ ሊዘረፉ የነበሩ 55 ታብሌት ስልኮች፣ 1 ኮምፒዩተር፣ 1 ፕሪንተር፣ 1 ሞተር ሳይክል፣ 10 ላፕቶፕ እና 100 ኩንታል ሲሚንት ከምዝበራ ማዳን የተቻለ ሲሆን እንዲሁም ያለአግባብ የተሰሩ 3 የሰው ሀይል ስምሪት ቅጥርና ዝውውር ማስቆምና ማሰረዝ የተቻለ መሆኑንም ተገልጿል።

በመሆኑም እነዚህ ብልሹ አሰራሮች የተከሰቱት በተለያዩ የግዥ ስርዓቶች፣ በንብረት አወጋገድ፣ በጫራታ አወጣጥ፣ ባልተገባ የደመወዝ አከፋፈል፣ በህገ ወጥ የቤት ማህበር አደረጃጀት፣ ያለአግባብ በተከፈለ አበል፣ ከህገ ወጥ የስሚንቶ ሽያጭ፣ ከህገ ወጥ የመሬት ወረራ እና ሌሎች ነፃ የህዝብ አገልግሎቶችን በገንዘብ በመቀየር የተገኙ ብልሹ አሰራሮችን በክትትሉ መሰረት ማግኘት ተችሏል ተብሏል።

በመጨረሻም በቀጣይ በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ በሂደት ላይ ያሉ ከመመሪያና ከአሰራር ውጭ እየተሰሩ ያሉ ብልሹ አሰራሮችንና ስርቆቶችን በአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ ለማስቆም ህብረተሰቡ በትክክለኛ ማስረጃ ላይ የተደገፈ ጥቆማዎችን በመስጠት የሀገርንና የህዝብን ሀብት ለማዳን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል በማለት ኮሚሽኑ መልክቱን አስተላልፏል።

## ሀገራዊ የሥነምግባር...

ከገጽ 1 የዞረ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ በበኩላቸው በከተማው ወጣቶችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን እና ህብረተሰቡን በማሳተፍ በተሰራው የቅንጅት፣ የንቅናቄና የፀረ-ሙስና ትግል ሥራ ሊመዘበር የነበረ 7 ቢሊዮን ብር የመንግስት እና የህዝብ ሀብት ከምዝበራ መታደግ መቻሉን ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ በከተማ አስተዳደሩ፣ በክ/ከተማ እና በወረዳ ባሉ መከታተያ ክፍሎች እንዲሁም በኮሚሽኑ 3 ሺህ 811 የሙስና ጥቆማ መቅረባቸውን ገልፀው ለሙስና በር ከፋች በሆኑ ተግባራት ውስጥ የተሳተፉ 2 ሺህ 751 በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ አካላት ተጠያቂ መሆናቸውን ገልጸዋል። ለሙስና ምንጭ የሆኑ አስተሳሰቦች፣ አመለካከት፣ የሥነምግባር ጉድለትና ብልሹ አሰራር ለመከላከል አሁንም የቅንጅት ስራ ላይ በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ በአስተሳሰብና አመለካከት የሚመጡ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን በመታገል ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱን የተናገሩት ደግሞ የሲዳማ ክልል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ ናቸው። በክልሉ 13 ዘርፎች በጥናት ተለይተው ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የሙስና መከላከል ስራ መሰራቱን አመልክተዋል። በተጨማሪም በክልሉ ገጠር አካባቢዎች በተለያዩ አካላት የተመዘበረ 59 ሺህ 482 ሄክታር መሬት እንዲሁም በከተሞች 16 ሺህ 856 ካሬ ሜትር መሬት ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ ተደርጓል ብለዋል።

በሥነምግባር ግንባታና ሙስናን ለመከላከል የወጡ ህጎች በተሻለ ደረጃ ተፈፃሚ ማድረጋቸውን የገለፁት ኮሚሽነሯ፤ በንግዱ ማህበረሰብ፣ በትምህርት ቤቶች፣ የፍትህ አካላትን ጨምሮ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በተሰራው የተቀናጀ ስራ ውጤት እየመጣ መሆኑን ገልፀዋል።

# ቬትናም በኮቪድ ወቅት ወደ አገራቸው ከሚመለሱ ዜጎች ከፍተኛ ጉቦ የጠየቁ ባለስልጣናት አሰረች

ቬትናም በኮቪድ-19 ወረርሽ ወቅት ወደ አገራቸው የሚመለሱ ዜጎችን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ጉቦ በመጠየቅ ሙስና ፈጽመዋል ያለቻቸውን ከፍተኛ ባለስልጣናት አሰራለች።

የሃገሪቱ የቀድሞ ሚኒስትርና ከፍተኛ ባለስልጣናትን ጨምሮ 54 ግለሰቦችን ከፍተኛ ሙስና በመፈጸም ወንጀለኛ ናቸው ሲልም የቬትናም ፍርድ ቤት ብያኔ አስተላልፏል። ባለስልጣናቱ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ወደ አገራቸው መመለስ ከሚፈልጉ የቬትናም ዜጎች ገንዘብ መመዝበራቸውንም ዳኛዎቹ ተናግረዋል። አንድ የቀድሞ ሚኒስትር ከ900 ሺህ ዶላር በላይ ጉቦ በመቀበል የ16 ዓመት እስር ተፈርዶባቸዋል።



የፍርድ ቤቱ ውሳኔ መንግሥት በአስተዳደሩ ላይ የታየውን ሙስና ለማስወገድ የከፈተው ዘመቻንም ተከትሎ ነው። ከሁለት ሳምንታት በላይ በፈጀው የፍርድ ሂደት የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ጨምሮ በርካታ የቀድሞ ባለስልጣናት፣ ከፍተኛ ዲፕሎማት ጉቦ በመቀበል፣ በማጭበርበር እና ስልጣናቸውን ያላግባብ በመጠቀም ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል።

ባለስልጣናቱ፣ ዲፕሎማቱና ተባባሪዎቻቸው በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት የንግድ በረራዎች መከልከላቸውን ተከትሎም ወደ አገራቸው መመለስ የሚፈልጉ የቬትናም ዜጎች ከፍተኛ ገንዘብ በመቀበልም መልሰዋቸዋል ተብሏል።

የመንግሥት ጋዜጣ የሆነው ቪቲሲ እንደዘገበው 25 የመንግሥት ባለስልጣናት በድምሩ 7 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር ጉቦ በመቀበል ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል። በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በጤና እና የህዝብ ደህንነበት ሚኒስቴር ውስጥ ባሉ በአራት ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይም የእድሜ ልክ እስርም ተበይኖባቸዋል። በዚህም የሙስና ወንጀል ላይ ነጋዴዎችና ግለሰቦችም ተባባሪ እንደነበሩ ተመላክቷል።

ማህበራዊ ሚዲያዎችን ጨምሮ ሌሎች ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት ተመላሾች ወደ ቬትናም ለመግባት ውድ የበረራ ዋጋን ጨምሮ በርካታ ውስብሰብ ሂደቶች እንዳጋጠማቸው ነው። አንዲት እናት ልጃቸውን ከአውሮፓ ወደ ቬትናም ለማምጣት 12 ሺህ ዶላር መከፈል እንደነበረባቸው ተነግሯል።



# በሶማሌ ክልል

## ግብርን በዲጂታል የግብይት ስርዓት በመሰብሰብ ብልሹ አሰራርን መከላከል መቻሉን የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ገለፀ

የሶማሌ ክልል ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ከኢቢሲ ሳይበር ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቆይታ፥ ክልሉ በ2015 በጀት ዓመት ከ9.7 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን ገልፀው፤ ይህም ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው በ8 በመቶ ብልጫ አለው ብለዋል። ይህን እቅድ ለማሳካት በክልሉ ከፍተኛ የገቢ ማሰባሰብ ንቅናቄ መከናወኑ፣ እንዲሁም አመራሩ እና የዘርፉ ሰራተኞች በየወሩ የአፈፃፀም ግምገማ ማከናወናቸው ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል።

አቶ አብዱልአዚዝ በገቢ ማሰባሰብ ንቅናቄው ከታቀደው 9 ቢሊዮን ብር በላይ 1 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ገቢ ለማሰባሰብ ታቅዶ ተሰርቷል ያሉ ሲሆን፤ ንቅናቄው 79.5 በመቶ ግቡን በመምታቱ ከ9.79 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ገልፀዋል። በ2015 በጀት ዓመት ግብር በዲጂታል የክፍያ ስርዓትም መከፈል መጀመሩን ያነሱት ኃላፊው፤ የክልሉ ማህበረሰብ ከዲጂታል ግብይት ጋር የተላመደ በመሆኑ አላስፈላጊ የስራ ጫናን በመቀነስ ሁሉም ሰው በያለበት ወረፋ ሳይጠብቅ መስተናገድ ችሏል ማለታቸውን የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን ዘግቧል።

ይህ የክፍያ ስርዓት የተገልጋዩን ብሎም የአገልግሎት ሰጪውን ጊዜ ከመቆጠቡም በላይ ብልሹ አሰራርን በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ ሆኗልም ነው ያሉት ኃላፊው። በዲጂታል የግብር ክፍያ ስርዓቱ ቅሬታ በማቅረብ ምላሽ እስከማግኘት የሚያስችል አሰራር መዘርጋቱን ጠቁመው፤ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ቴሌኮም እና ሄሎ ካሽ ጋር በትብብር እየተሰራበት ይገኛል ብለዋል። አክለውም፥ ክልሉ ካለው ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ አኳያ ከዚህ በላይ ገቢ መሰብሰብ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦ በ2016 ዓ.ም የገቢ አሰባሰብ ስርዓቱን ይበልጥ በማዘመን 16 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል ብለዋል።



# በ25 ዘርፍ ተቋማት ስር ለሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች የዝግጅት ምዕራፍ ሥልጠናዊ ውይይት ተካሄደ

በ25 ዘርፍ ተቋማት ስር ለሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በ2015 በጀት አመት ሀገራዊ የሙስና መከላከል የአፈጻፀም ሪፖርት እና በ2016 በጀት አመት የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሀገራዊ እቅድ ላይ ያተኮረ የአራት ቀናት ሥልጠናዊ ውይይት ተካሄደ።

በተካሄደው ውይይት የ2015 በጀት አመት ሀገራዊ የሙስና መከላከል የአፈጻፀም ሪፖርት እና በ2016 በጀት አመት የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሀገራዊ እቅድ እንዲሁም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የ2016 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ማስፈፀሚያ ሥልቶች ላይ ለአራት ቀናት ሲሰጥ የነበረው ሥልጠናዊ ውይይት የጋራ ሀሳብ የተያዘበት መሆኑ ተገልጿል።



የሥልጠናዊ ውይይቱ ዓላማ በ25 ዘርፎች የሚገኙ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ወጥ የሆነ እቅድ እና ሪፖርት እንዲሁም የጋራ አሰራር እንዲኖር ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ተመላክቷል።

# ከህብረተሰቡ በቀረቡ የሙስና ወንጀል ...

ከገጽ 1 የዞረ

ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በሪፖርታቸው ብልሹ አሰራርን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንፃር ሰፊ ስራዎች ተሰርቷል ማለታቸውን ገልፆ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዘግቧል። በሀሰተኛ ሰነድ ማጭበርበር፣ ጉቦ በመቀበል፣ በግገርና ጨረታ ማጭበርበር በሌሎች ተያያዥ ወንጀሎች በተሳተፉ ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርጃዎች እንደተወሰዱም አመላክተዋል። በክልሉ 24 ሺ ከሚጠጉ ሠራተኞች ሠነድ ወደ 2 ሺህ 241 ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የያዙ ሠራተኞችና አመራሮች መገኘታቸውን መዘገባችን ይታወቃል።

# በበጀት ዓመቱ 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር የተመዘበረ ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና ማስመለስ ተችሏል

**- አቶ ሽመልስ አብዲሳ**




በሙስና የተመዘበረው የህዝብ ሀብት ከማስመለስ አኳያ በበጀት ዓመቱ 2.6 ቢሊዮን ብር መታገዱን እንዲሁም 1.1 ቢሊዮን ብር የተመዘበረ ገንዘብ ወደ መንግሥት ካዝና መመለሱን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገልጸዋል።

አቶ ሽመልስ አብዲሳ አክለውም 454 የሙስና ጥቆማዎች ላይ የማጣራት ስራ እየተከናወነ መሆኑንም በአዳማ ከተማ በተካሄደው የጨፌ 5ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ ለተገኙ የጨፌው አባላት አብራርተዋል። የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥን ይበልጥ ለማረጋገጥ ዲጂታላይዜሽንና የአሰራር ስርዓት ማዘመን የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክሮ የሚቀጥሉ መሆኑንም በሪፖርታቸው አመልክተዋል።

# የታማኝነት ሽልማት ፕሮግራም ተካሄደ






ታማኝ ሰዎችን ማበረታታት እንዲሁም በሌሎች ሰዎች መነሳሳትን መፍጠር ዓላማው ያደረገ የታማኝነት ሽልማት በብሔራዊ ትያትር ተካሂዷል።

የፕሮግራሙ አዘጋጅ እና የቫልዩ በጎ አድራጎት የልማት ድርጅቶች ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ያሬድ ተስፋዬ ፕሮግራሙ ሙስናን ለመዋጋት እና በስነምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል።

ለሽልማት እጩ ሆነው የቀረቡት በተለያየ ምክንያት የወደቁ ወይም የጠፉ ንብረቶችን አግኝተው በታማኝነት ለፀጥታ አካላትና ለሚመለከተው ተገቢ ተቋም ያስረከቡ 17 ግለሠቦች ሲሆን ከተሸላሚዎቹ መካከል አቶ ጌትነት ተሾመ በቂርቆስ ክ/ከተማ 2,000 ብር፣ ናሆም ደምሴ በቂርቆስ ክ/ከተማ 2 ሞባይል፣ አቶ ፍቅሬ ግዛው እና ተሾመ ፀጋዬ በኮልፌ ክ/ከተማ ላፕቶፕ አግኝተው በመመለስ፤ አቶ ገብረእየሱስ ገና በጉለሌ ክ/ከተማ በስህተት በአቢሲኒያ ባንክ አካውንታቸው ላይ የገባላቸውን 743,000 ብር በመመለስ እንዲሁም አቶ በሽር አህመዲን በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መርካቶ አካባቢ 7,700 ብር አግኝተው በመመለስ መሆኑ ተጠቅሷል።

# የሲዳማ ክልል ምክር ቤት ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የህዝብ ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ ጥረት አድርጓል

**- ዋና አፈ ጉባዔ ፋንታዬ**

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የህዝቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በአግባቡ ለመመለስ ጥረት ማድረጉን የሲዳማ ክልል ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ፋንታዬ ከበደ አስታወቁ።

የምክር ቤቱ አባላት በየደረጃው ድጋፍና ክትትል በማድረጋቸው በበጀት ዓመቱ የልማት ሥራዎች አፈፃፀም አበረታች ውጤት መመዝገቡን አስታውቀዋል። ምክር ቤቱ አስፈጻሚ አካላትን በመገምገም፣ ድጋፍና ክትትል በማድረግና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል አጥፊዎች በህግ እንዲጠየቁ መስራቱንም ወ/ሮ ፋንታዬ ገልጸዋል። ምክር ቤቱ በበጀት ዓመቱ ባከናወናቸው የድጋፍና ክትትል ሥራዎች አፈጻጸማቸው ደከም ያሉ አመራሮች ከኃላፊነት እንዲነሱና በሌሎች ጠንካራ አመራሮች እንዲተኩ መደረጉን ዋና አፈ ጉባዔዋ አስረድተዋል።




የምክር ቤቱ አባላት ወደ መረጣቸው ህዝብ ወርደው በማወያየት የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በአግባቡ ምላሽ እንዲያገኙ ተግተው መሥራታቸውን ገልጸው፣ በክልሉ የህብረተሰቡ ቅሬታ ሆኖ የቆየው የዞን አደረጃጀት በቅርቡ ምላሽ ማግኘቱን መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል። የክልሉ ምክር ቤት አባላት የህዝብ እንደራሴ እንደመሆናቸው መጠን የሚጠበቅባቸውን የህዝብ ውክልና በአግባቡ እንዲወጡም የሲዳማ ክልል ምክር ቤት 6ኛ ዙር 3ኛ የስራ ዘመን 5ኛ መደበኛ ጉባኤ በሀዋሳ በተካሄደው መድረክ አሳስበዋል።

# የኮሚሽኑ አመራሮችና ሰራተኞች አረንጓዴ አሻራቸውን አስቀመጡ

የፌደራል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮችና ሰራተኞች በሀገር አቀፍ ደረጃ ‹‹ነገን ዛሬ እንትከል›› በሚል መሪ ቃል በአንድ ጀንበር 500 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል በተያዘው እቅድ መሰረት የአረንጓዴ አሻራቸውን አስቀምጠዋል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብሩ የተካሄደው በኢፌዴሪ መከላከያ ጠቅላይ መምሪያ ሲሆን፥ በዚህ መርሃ-ግብር የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሰራተኞች ተሳትፈዋል። በተያያዘ መረጃ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ተጠሪ ከሆኑ አቻ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በሸገር ከተማ ፉሪ ክፍለ ከተማ የክረምት በጎ ፈቃድ ስራ አስጀምረዋል። በመርሐ-ግብሩ የአቅመ ደካሞች ቤት እና የትምህርት ቤት እድሳት፣ የችግኝ ተከላ እና ሌሎች የበጎ ፍቃድ ስራዎች አከናውነዋል። የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ከመስክ ስራቸው ጎን ለጎን በባሌ ዞን አጋርፋ ወረዳ የአረንጓዴ አሻራ 500 ሚሊዮን ችግኝ በአንድ ጀምበር መርሐ ግብር አሻራቸውን አስቀምጠዋል።





# የ2015 በጀት አመት የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ተግባራት ዳሰሳ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሰጠውን የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተልዕኮ በብቃት ለማሳካት በ2015 በጀት አመት በአዲስ አደረጃጀት እና አሰራር ወደ ስራ መግባቱ ይታወሳል። ከተጀመሩ አዲስ አሰራሮች መካከል ተግባራትን በዘርፍ ደረጃ መምራት ይጠቀሳል። ከዚህ አንጻር በፌደራል እና በክልሎች በዋና ዋና የስራ ክፍሎች የተከናወኑ ተግባራትን የዚህ ወር ዋና የትኩረት ማዕከል በማድረግ ለመቃኘት ተሞክሯል።

# የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አቅም ማሳደግ

ኮሚሽኑ በፌደራል መንግሥት ተቋማት፤ በልማት ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ተቋማት የተመደቡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች፤ የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ሥራዎችን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ፤ ክትትል እና ግምገማ ያደርጋል፡፡ የኮሚሽኑ ተልዕኮ በየተቋማቱ በተደራጁ የሥራ ክፍሎች አማካኝነት በአግባቡ እንዲከናወን፤ በሥልጠና እና በሱፐርቪዥን ሥራዎች አቅም የመገንባት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ ለ100 የሥነምግባር መከታተያ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲወስዱ አስቻይ ሁኔታ መፍጠርና የብቃት ምዘና ማከናወን መቻሉን ከሪፖርቱ ማየት ተችሏል፡፡

በ25 ዘርፎች የፌደራል ተቋማት፤ የክልሎችና የከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች ዕቅድ፤ ሪፖርት እና ግብረ-መልስ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ አገር ዓቀፍ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ስታንዳርድ አደረጃጀት በማጥናት ምክረ ሐሳብ እና ሞዴል አደረጃጀት በማዘጋጀት የባለድርሻ ዉይይት መተግበር ተችሏል፡፡ ሌላው በዘርፍ-ተኮር ደረጃ በ22 ዘርፎች ስር በሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን መረጃ ማደራጀትና ዘርፍ-ፎረም ለማቋቋም በታቀደው መሰረት በ13 ዘርፎች ማቋቋም መቻሉንም ከእቅድ አፈጻፀም ሪፖርቱ ለማየት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ዘርፍ ተኮር ሀገራዊ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች የዲጂታል ትስስርና ትብብር ለመፍጠር በታቀደው መሰረት ትስስር በመፍጠር የ2015 መነሻ እቅድ በማዘጋጀት እና በመነሻ እቅድ ላይ ኦሮንቴሽን በመስጠት ዘርፎች የ2015 የበጀት አመት ዕቅድ እንዲልኩ መከታተል እና መደገፍ ተችሏል፡፡

የዘርፎች የ2015 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን እንዲልኩ መከታተል እና ዘርፍ ተኮር የአፈፃፀም ሪፓርት ማዘጋጀት፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተቋማዊ አቅምና ብቃት ምዘና እና ማረጋገጫ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ለመደገፍ እና ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስራ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ አራት መነሻ ሰነዶች ማዘጋጀትና ለዘርፎች መላክ ተችሏል፡፡ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በአደረጃጀት እና በአሰራር ሥርዓት ዙሪያ የሱፐርቪዥን ሥራ ማከናወን መቻሉን ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡

ሌላው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በ25 ዘርፎች እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲከበር በመከታተል፤ ሀገራዊ መረጃ በ24ቱ ዘርፎች መከታተል እና ሪፖርት ማደራጀት ሲሆን በተቋማት በተለየ መልኩ በንቅናቄ ማክበር መቻሉ ተገልጿል፡፡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ያላደራጁ ወይም የተጓደለ የሰው ሀይል ያላቸውን ተቋማት መከታተያ ክፍሎች እንዲያደራጁ/ እንዲያሟሉ መከታተል እና በመደገፍ፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያላደራጁ ክልሎችና ከተሞች እንዲያቋቁሙ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች እንዲያቋቁሙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በፊት በኮሚሽኑ ሲሰሩ የነበሩ ተግባራት እና ኃላፊነትም በተገቢዉ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ የክልል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችና ከተማ መስተዳድሮች የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ውይይት መድረክ ለማዘጋጀት ታቅዶ፤ የታቀደዉን ማከናወን ተችሏል፡፡ በ25 ዘርፎች የዘርፍ-ፎረም የዲጂታል ትስስር በማጠናከር የመረጃ ልዉዉጥ ቀልጣፋ በማድረግ፤ ብሔራዊ የጸረ-ሙስና ትግል ሳምንታዊና ወቅታዊ አዝማሚያ ግምገማ ሪፖርት ለማኔጅመንት ኮሚቴ በ6ቱ ዘርፎች መላክ መቻሉም ሪፖርቱ ያመለክታል፡፡ ሌላው የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ አስፈጻሚዎች አቅም ግንባታ ክፍል የሚመራበት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች የአቅም ግንባታ ስራ ማስፈፀሚያ ፕሮቶኮል ማዘጋጀት ሲሆን ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

በአጠቃላይ ከስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ክትትልና ድጋፍ አንጻር የ2015 በጀት ዓመት የትዉልድ ሥነምግባር ግንባታ ለማከናወን የተመረጡ የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥልጠናዎች፤ የግንዛቤ ማጎልበቻ ሥራዎች እና የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች አቅም ማጎልበቻ ተግባራት በጥራት፤ በተገቢነት እና በተደራሽነት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሥር ካሉ ኮሚሽኖች ጋር በቅንጅት በመሥራት የትዉልድ ሥነምግባር ማነጹን ሥራ እንዲሰፋ እና ዉጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሪፎርም ሥራዎችን በተከታታይ በማከናወን የፕሮግራሙ ዓላማ እና ግቦች እንዲሳኩ ርብርብ እንደሚደረግ እንዲሁም የትዉልድ ሥነምግባር ግንባታ ፕሮግራም፤ ዜጎች ሙስናን የማይታገሱ እና በጽናት የሚታገሉ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ ከወዲሁ ስትራቴጂክ አቅጣጫ ተዘርግቶ እየተሰራ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

# የሥነምግባር እና ሙስና መከላከል የግንዛቤ ማጎልበቻ

ኮሚሽኑ የሥነምግባር እና ሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሞጁል ላይ ተመስርቶ ሥልጠና ከመስጠት ባለፈ፤ ለህዝብ ተደራሽ የሚሆኑ የግንዛቤ ማጎልበቻ ሥራዎችን አቅዶ ሲያከናዉን ቆይቷል፡፡ የግንዛቤ ማጎልበቻ ሥራዉ ለሕዝብ በቀጥታ ተደራሽ የሚደረጉ አገርዓቀፍ ተግባራት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የዜጎችን ሥነምግባር የሚያንጹ እና ሙስናን በራስ ዓቅም እንዲታገሉ ዘርፈ-ብዙ የባለድርሻ አካላት በውይይት መድረክ ተገኝተዉ ግንዛቤ ሰጪ ሐሳቦችን እንዲያነሱ ማድረግ እና በሚዲያዎች አማካኝነት ውይይቱን ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ፤ እንዲሁም ሌሎች የሚዲያ ፕሮግራሞችን በመጠቀም ትዉልዱ ስለሥነምግባር እና ሙስና መከላከል አጋዥ የሆኑ መልዕክቶችን ማስተላለፍን ያካትታል፡፡

በዚሁ መሰረት ባሳለፍነው በጀት አመት በየወሩ በባለሙያዎች አማካኝነት የዉይይት መነሻ ሰነድ (Discussion Papers) የማዘጋጀት ሥራዎችን ማካሄድ፤ ሙሉ የውይይት ሐሳቦችን በኢቢሲ ቴሌቪዥን ፕሮግራም ቀርጾ የማስተላለፍ ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በርካታ ዜጎች የሚከተሉትን፤ የኮሚሽኑን የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ በመጠቀም በየዕለቱ ግንዛቤ ሰጪ እና ትምህርታዊ መልዕክቶችን የማሰራጨት ተግባራትን ማከናወን ተችሏል፡፡ የግንዛቤ ማጎልበቻ ፕሮግራም ዋናዉ ዓላማ ሕዝቡ በፀረ-ሙስና ትግሉ አጋርነት እንዲያረጋግጥ ተገቢዉን መረጃ በመስጠት እና በማነቃቃት ማታገል ነዉ፡፡

የባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማጎልበቻ ውይይት ለማከናወን ታቅዶ ጥራት እና ተገቢነት ያላቸውን ሰነዶች በማዘጋጀት የግንዛቤ ማጎልበቻ ስራዎችን መስራት ተችሏል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 5ቱ በኢቲቪ የተላለፉ ሲሆን ሶስቱ ደግሞ ፕሮሲዲንግ ተዘጋጅቶላቸው ተሰንደዋል፡፡ በተለይም ከኮሚሽኑ ተልዕኮ እና ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር አንገብጋቢ አጀንዳዎችን ትኩረት ማድረግ በማስፈለጉ፤ ሌሎች አምስት ርዕሰ-ጉዳዮች ለግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት ፕሮግራም ተደራሽ ያልተደረጉ ሲሆን የዉይይት ሰነድ አዘጋጅ ባለሙያዎችን አቅምና ብቃት ለማሻሻል ሥልጠና የብቃት ምዘና ማከናወን መቻሉን ሪፖርቱ ያሳያል፡፡

ሌላው በበጀት ዓመቱ የጥበብ ስራዎችን በመጠቀም ለህፃናት፣ ለወጣቶችና ለቤተሰብ አባላት ግንዛቤ መፍጠሪያ መልዕክቶችን በሚዲያ ማስተላለፍ ሲሆን ቤተሰብ፣ ወጣቶችን እና ልጆችን የተመለከቱ የሥነምግባር ጉዳዮችን በጥያቄ እና መልስ በማካተት ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ከ600 በላይ በሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች የጥያቄና መልስ ውድድር በማካሄድ በዋልታ ቴለቪዥን በ32 ክፍል ማሰራጨት ተችሏል፡፡ የግንዛቤ ማጎልበቻ ፕሮግራም ተጽዕኖ በተመለከተ አገርዓቀፍ የባለድርሻ አካላት ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት በማዘጋጀት የግንዛቤ ማጎልበቻ ፕሮግራም ሥራዎችን በሰነድ ደረጃ ለማደራጀት ተችሏል

የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የሚመራበት የጥራት እና ተገቢነት ግምገማ ፕሮቶኮል በማዘጋጀት ሥራ ላይ ለማዋል በታቀደው መሰረት ማከናወን ተችሏል፡፡ የሥነምግባር እና ሙስና መከላከል የግንዛቤ ማጎልበቻ ሥራዎች ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ሥር ባሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች አማካኝነት ጭምር ሰፊ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል፡፡

# የሥነምግባር እና የሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥልጠና

የሥነምግባር እና የሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥልጠና ጥራት፤ ተገቢነት እና ተደራሽነት ማሳደግን በተመለከተ ከዚህ በፊት ያለበቂ የጥራት እና የተገቢነት ማረጋገጥ ሥርዓት፤ የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠና ሲሰጥ የነበረዉ በዚህ በጀት ዓመት ደረጃዉን በጠበቀ ሞጁል ላይ እንዲመሰረት የአሠራር ሥርዓት እና የሥልጠና ሥነዘዴ የማሻሻል ሥራዎች መከናወኑን ሪፖርቱ አመላክቷል። የሥልጠና ሞጁል ጥራት እና ተገቢነት ማረጋገጫ ፕሮቶኮል በውጭ አማካሪዎች ድጋፍ ተዘጋጅቶ እና ባለድርሻ አካላት ግምገማዎች ተካሂዶ ከፀደቀ በኋላ፤ ሥራ ላይ እንዲዉል በማድረግ ከዚህ በፊት ሥራ ላይ የነበሩ ሞጁሎች በሙሉ በገለልተኛ አካላት መገምገሙን በሪፖርቱ ተመላክቷል። የጥራት እና የተገቢነት ደረጃቸዉም ተፈትሾ፤ በፕሮቶኮሉ ምዘና ደረጃ እንዲሻሻሉ መደረጉን ሪፖርቱ ያሳያል።


የሥነምግባር ... ወደ ገጽ 6 የዞረ

# ምሩቃን በሥነምግባር የታነፁ ከአድልኦ የፀዱ ሁሉንም እኩል የሚያገለግሉ የመልካም ስብዕና ተምሳሌት እንዲሆኑ እና ከሙስናና ከብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ ህዝባቸውን ማገልገል እንዳለባቸው ተገለፀ።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለያዩ መርሀ ግብሮች ሲያስተምሯቸው የነበሩ ተማሪዎቻቸውን አስመርቀዋል። ምሩቃን በሥነምግባር የታነፁ ከአድልኦ የፀዱ ሁሉንም እኩል የሚያገለግሉ የመልካም ስብዕና ተምሳሌት እንዲሆኑ እና ከሙስናና ከብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ ህዝባቸውን ማገልገል እንዳለባቸው የሴቶችና የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጸዋል።

የትምህርት ሚኒስቴር ምንስትር ዴኤታ ዶ/ር ሳሙዔል ክፍሌ በበኩላቸው ሌብነትን የሚፀየፍ እና ሥነምግባር ያለው ሲቪል ሰርቫንት እንዲገነባ ምሩቃን የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው ብለዋል። ምሩቃን ወደ ስራ ሲሰማሩ ራሳቸውን ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በመጠበቅ አገርን እና ህዝብን በቅንነትና በታማኝነት ማገልግል እንዳለባቸው የተናሩት ደግሞ የደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉስ ታደሰ ናቸው፡







# በሐረሪ ክልል ተመዝብሮ የነበረ 35 ሚሊየን ብር የመንግስትና የህዝብ ሀብት እና ከ17 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት እንዲመለስ ተደረገ



በሐረሪ ክልል ተመዝብሮ የነበረ 35 ሚሊየን ብር የመንግስትና የህዝብ ሀብት እና 17 ሺህ 500 ካሬ ሜትር መሬት ማስመለስ መቻሉን የክልሉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስታወቀ።

የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ ሃላፊ አቶ አዩብ አሕመድ እንዳሉት፥ በክልሉ በመንግስት ተቋማት ለሙስና እና ለመልካም አስተዳደር መበላሸት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በመለየት በትኩረት ተሰርቷል። በዚህ መሰረትም በመሬት ነክ ጉዳዮች፣ በገቢና ታክስ፣ በፍትሕ፣ በፕሮጀክቶች እና ግዢ ዘርፎች ላይ በትኩረት መሰራቱን ነው የገለጹት።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ምርመራቸው ተጠናቆ ለፍርድ ቤት ከቀረቡት 1 ሺህ 374 መዛግብት ውስጥ 720ዎቹ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ጠቁመዋል። ከሙስና ጋር በተያያዘ መንግስት ሊያጣው የነበረ ከ35 ሚሊየን ብር በላይ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ማስመለስ መቻሉን አቶ አዩብ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ተናግረዋል።

በተመሳሳይ በሕገ-ወጥ መንገድ በግለሰቦች ተይዞ የነበረ 17 ሺህ 500 ካሬ ሜትር መሬት እንዲመለስና ወደ መንግስት መሬት ባንክ ገቢ መደረጉን ጠቅሰዋል። የሕዝብ ሃብትን በክስና በድርድር ከማስመለስ አንጻርም 22 ሚሊየን ብር በላይ በድርድር ማስመለስ መቻሉንም አስረድተዋል።

ከገጽ 5 የዞረ

# የሥነምግባር እና የሙስና...

በዚህም መነሻነት አስራ አራት ሞጁሎች ክለሳ በማጠናቀቅ ለሥልጠና እንዲዉሉ ተደርጓል:: ቀሪዎች ሶስት ሞጁሎች የግምገማ ሂደቱ እየተጠናቀቀ ስለሆነ፤ በቀጣይ በጀት ዓመት ለሥልጠና ሥራ እንደሚውሉ ተገልጧል:: ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ በአገርዓቀፍ ደረጃ የሚከናወኑት የትዉልድ ሥነምግባር ግንባታ ሥልጠናዎች ሥርዓተ-ሥልጠና እንዲኖራቸዉና የሥልጠናዉ ዉጤታማነት ተገማች እንዲሆን አቅዶ ሲሰራ የቆየ ሲሆን በዚህም መሰረት፤ በበጀት ዓመቱ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ስልጠና፤ የግምገማ ሂደቱን በማጠናቀቅ ለቀጣይ ዓመት ሥራዎች ዝግጁ ተደርጓል:: በአገርዓቀፍ ደረጃ የትዉልድ ሥነምግባር ግንባታ ስልጠና ዉጤታማነት እንዲኖረዉ ወጥነት ያለዉ አሠራር መዘርጋት ተችሏል:: የትዉልድ የሥነምግባር ግንባታ የሥልጠና ተግባር በዋናነት፤ የአመለካከት ለዉጥ ማምጣት ያለበት በመሆኑ፤ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ከተጨባጭ የሥነምግባር ችግሮች የመነጩ እንዲሆኑ ማድረግ አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነዉ:: በመሆኑም ኮሚሽኑ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት በሁሉም ዘርፎች በማካሄድ የሥልጠና ፍላጎትን ጨምሮ እየለየ ቆይቷል::

ከአገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር፤ የንግዱን ዘርፍ የገበያ ዝንፈት ጋር ተያይዞ እየተፈጠረ ያለዉን የሙስና እና የአሠራር ሥርዓት ብክነት የክትትል ሥራ እንዲጠናከር የንግድ ዘርፍ አስቸኳይ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ፤ የንግድ ዘርፍ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ሥልጠናዊ ዉይይት ማድረግ በመቻሉ ከታቀደው በላይ መፈፀም መቻሉን ለማየት ተችሏል:: በተጨማሪም የዘርፎቹ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተሻለ ግንዛቤ በማግኘታቸዉ፤ በከፍተኛ መነቃቃት በየዘርፋቸዉ የሚከናወኑ የፀረ-ሙስና ትግል ስራዎችን ለማጠናከር ዕድል መፍጠር ተችሏል::

የሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ ባለሙያዎችን ለብሔራዊ የፀረ-ሙስና ትግል አጋዥ እንዲሆን ለ88 አሰልጣኞች ስልጠና እና ብቃት ምዘና ተከናዉኗል:: የጥራት እና የተገቢነት ግምገማ መስፈርት ያሟሉ እና የፀደቁ ሞጁሎችን በመጠቀም በሙስና ሥጋት ጥናት ሪፖርት መሰረት ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ የተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች የሥነምግባር ሥልጠና እና ሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ስልጠና ለ151 ግዥ ዳይሬክተሮች እና በሁለት ዙር በቁጥር ለ602 ለተቋማዊ ለውጥ፣ ለህግ አገልግሎት፣ ለስነምግባር መከታተያና ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክተሮች በአጠቃላይ ለ753 ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል:: ከዚህ ሥልጠና በመነሳት በሁሉም ተቋማት ያሉ የህግ አገልግሎት፣ የውስጥ ኦዲት፣ የሥነምግባር መከታተያ እና የተቋማዊ ለዉጥ ሥራ ክፍሎች የጋራ ተቋማዊ ፎረም እንዲፈጥሩ እና በየተቋሞቻቸዉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ሙስና በቅንጅት እንዲከታተሉ አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ የተቋማት መሪዎችም ይህን አሠራር በቅንጅት ድጋፍ እንዲያደርጉ በደብዳቤም ጭምር ማሳወቅ መቻሉን ሪፖርቱ ያመለክታል::

ሌላው በበጀት አመቱ ከስልጠና አንጻር ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ የሥልጠና ክፍል ፋሲሊቲ ማሟላት ሲሆን የሥርዓተ-ሥልጠና እና ሞጁሎችን በማጠናቀቅ ሥራዎች በበየነመረብ እየተቀረጹ ለሚተላለፉት ሥልጠናዎች ዋና ዋና ግብዓት ስለሆኑ፤ እነዚህን ተግባራት ማጠናቀቅ ተችሏል:: በተጨማሪም ኮሚሽኑ ከ International Anticorruption Academy-IACA ጋር በፈጸመዉ የትብብር ስምምነት መሰረት በቀጣይ 11 የሥልጠና ማዕከል/አካዳሚ በመጠቀም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ትምህርት እና ሥልጠና እንዲከታተሉ እየሰራ ይገኛል:: በስምምነቱ መሰረት በቅናሽ ክፍያ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በፀረሙስና ትምህርት ዙሪያ የሁለተኛ ድግሪ ትምህርት ዕድል IACA እንዲሰጣቸዉ ጥሪ ተደርጎ በዉድድር ሂደት ላይ

በስነምግባር መከታተያና ማስተባበሪያ የስራ ክፍል ለቀረቡ 507 የሥነምግባር አስፈፃሚዎች፤ እንዲሁም 7 ፕሮጀክቶችን ለሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የዓቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ተችሏል::


በተጨማሪም የኮሚሽኑ ባለሙያዎች እና በየተቋማት የተመደቡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ሠራተኞች በየተቋሞቻቸዉ ተልዕኳቸዉን በብቃት እንዲያከናወኑ የአሰልጣኝነት ሥልጠናዎችን መስጠት ተችሏል:: በቀጣይ የሥልጠና ሞጁሎችን ጥራት፤ ተገቢነት እና ብዛት ማሳደግ፤ ሥልጠናዎችን ለከፍተኛ አመራሮች እና ምክር ቤት አባላት ጭምር ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በበየነመረብ አማካኝነት ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ በትኩረት ይሰራል:: የሥነምግባር ግንባታ ሥልጠና የአመለካከት ለዉጥ እያመጣ ስለመሆኑ፤ ክትትልና ግምገማ ማድረግ በትኩረት ይሰራል::



# የሙስና መከላከል ጥናት ሥራዎች

ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ሥራዎች መረጃ እና ዕዉቀት-መር እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ጥናት ንዑስ ፕሮግራም በአዲስ መልክ ቀርጾ ሥራ ላይ አዉሏል። የዘርፍ-ተኮር አሠራር ሥርዓት የተዘረጋበትም ዋናዉ ምክንያት፤ በአንድ ዘርፍ ያለዉን አጠቃላይ የልማት ሥራዎችን ሊያደናቅፍ የሚችል እና ዘርፉ በሁሉም የአስተዳደር ወሰን (ከፌደራል እስከ ታችኛዉ መዋቅር) ውጤታማ እንዳይሆን ሊያደናቅፍ የሚችል የሙስና እና የአሠራር ሥርዓት ብክነት ክትትል ለማድረግ እና መረጃ ለማመንጨት የፖሊቲካ እና የመንግሥት ሥራ አመራሩን በማማከር በቁርጥኝነት የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰድ አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር ያለመ ነዉ።

በዘርፍና በሥሩ ያሉ አመራሮች እንዲሁም ሰራተኞች፤ የዘርፉን እና የተቋማትን የሙስና እና የአሠራር ሥርዓት ብክነት በተመለከ በገለልተኛ አካል የተጠናዉን መረጃ መነሻ በማድረግ፤ በየራሳቸዉ አቅም ሙስና እንዲታገሉ እና የአሰራር ሥርዓት ብክነት ምጣኔ እንዲቀንሱ ማገዝ ይሆናል። በተጨማሪም፤ ኮሚሽኑ የጥናቱን ግኝነት መነሻ በማድረግ የሥልጠና ሥራዎችን፤ የግንዛቤ ማጎልበቻ እና የሀብት ምዝገባ ተግባራትን በትኩረት ይሰራል። በመሆኑም፤ በበጀት ዓመቱ በ22 ዘርፎች፣ በምክር ቤቶችና በአስተዳደር ዘርፍ በድምሩ በ23 ዘርፎች ደረጃ አዲስ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት ማካሄድ እና በ2014 በጀት ዓመት የተከናወኑትን የሶስት ዘርፎች ጥናት ለየዘርፎቹ/ለተቋማቱ መሪዎች ግንዛቤ የመፍጠር እና የሙስና መከላከያ ምክረ ሐሳብ በማቅረብ ክትትል የማድረግ ሥራዎች ተከናዉኗል።




**የክልሎች እና የዘርፍ ተቋማት አፈጻፀም**

ዘርፍ-ተኮር ሙስና ሥጋት ጥናት በማካሄድ የሙስና መከላከል ምክረ-ሐሳብ ማመንጨትና ክትትል ማድረግ በ22 ዘርፎች ላይ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት ማከናወን የተቻለ ሲሆን ተጠንተው በተጠናቀቁ በ3 ዘርፎች ላይ ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ጥናት ምክረ ሃሳብ ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን ሪፖርቱ ያሳያል። በበጀት ዓመቱ በ22 ዘርፎች የዘርፍ-ተኮር የተካሄዱና የተጠናቀቁ የሙስና ሥጋት ጥናት ሪፖርቶችን በዲጂታል አማራጭ ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን የተወሰኑትን ኮፒ የማሳተም ሥራ እንደሚሰራ ተገልጧል።

ኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ችግር-ፈቺ እና ለብሔራዊ የሙስና መከላከል ፕሮግራም ግባዓት የሚሆን ለማድረግ፤ በተሻሻለ የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን በተለይም፤ ዘርፍ-ተኮር ጥናት በመሆኑ፤ የጥናቱ ሪፖርት በአንድ ዘርፍ ዉስጥ ያሉ ተቋማት በድምሩ ለዘርፉ ሊያመጡ የሚገባቸዉን የልማት ውጤታማነት በሙስና እና በአሠራር ሥርዓት ብክነት እንዳይሰናከሉ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር እና የፖለቲካ እና የመንግስት ሥራ አመራሮች በዘርፉ ያሉ የሙስና ሥጋቶችን ቀድመዉ በመገንዘብ በራሳቸዉ አቅም የሰላ የፀረ-ሙስና ትግል እንዲያከናዉኑ ዕድል እየፈጠረ ይገኛል። በዚህ በጀት ዓመት፤ የምሁራን ተሳትፎ ተጨምሮበት፤ በ22 ዘርፎች (በፌደራል መንግሥት ደረጃ) የሙስና ሥጋት ጥናት ማከናወን ተችሏል።

የጥናት ሪፖርቱ ላይ የባለድርሻ አካላት ዉይይቶችን በማካሄድ ጥናቱ የመጨረሻ ቅርጽ እንዲይዝ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም፤ ጥናት ሪፖርቶችን ለዘርፍ መሪዎችና ባለሙያዎች በንቅናቄ ዉይይት መድረክ አማራጭ በማካሄድ፤ የዘርፎች የሙስና መከላከል ዕቅድ እና ትግበራ ሥራዎች መረጃ መር እና የተቀናጀ እንዲሆን ክትትል ይደረጋል። ኮሚሽኑም የሙስና ሥጋት ተብሎ በተለዩ በየዘርፉ ያሉ ግኝቶችን መነሻ በማድረግ ከፍተኛ ሥጋት በሆኑ ጉዳዮች የአሠራር ስርዓት ግልጽነት ጥናት ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ለማካሄድ ትኩረት ያደረጋል። የሀብት ምንጭ የማጣራትና ሌሎችም የሙስና መካለከል ሥራዎች ትኩረት እንዲሰጡ አቅጣጫ የማመላከት ሥራዎች በበጀት ዓመቱ ተከናዉኗል።

# የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች

የአስቸኳና መከላከል ሥራ ከዚህ በፊት በተግባር ደረጃ የነበረዉን በማሻሻል በንዑስ ፕሮግራም ደረጃ አደረጃጀት እና አሰራር ሥርዓት በመከለስ በበጀት ዓመቱ ሰፊ ሥራዎች ተከናዉነዋል:: የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ክትትል በማድረግ ሙስና እንዳይፈጸም፤ ሀብት እንዳይባክንና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ማድረግ ሥራዎች በበጀት ዓመቱ በተገቢዉ ማከናወን መቻሉን ሪፖርቱ የሚያመላክት ሲሆን ከዜጎች የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ፤ ሙስና የመፈጸም ሂደቱን የማቋረጥ እና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ እንዲሁም ድርጊቱ ለቀጣይ ትምህርት እንዲሆን የምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራዎች በተመረጡ ግኝቶች ዙሪያ እንዲሰራ ጥረት ተደርጓል::

ሌላው 78 ጥቆማዎች ቀርበዉ፤ በሁሉም ላይ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ ተከናዉኗል:: በተሰራ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራ 3 ጊዜ ለህዝብ ይፋ የተደረገ መሆኑንም ሪፖርቱ ያሳያል:: ከአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራዎች መካከል በ5 ጉዳዮች ላይ የምርመራ ጋዜጠኝነት ተሰርቷል:: የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ ሙስና እንዳይፈጸም በሂደት ላይ እያለ በማቋረጥ የሚወሰድ እርምጃ በመሆኑ፤ ኮሚሽኑ ቀልጣፋ አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ በትኩረት እየሰራ ይገኛል:: በተጨማሪም፤ በክልል/ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች በኩልም ይኸዉ የአሠራር ሥርዓት ከፍተኛ ፋይዳ እያስገኘ ነዉ::

በቀጣይ፤ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎችን ክትትል የማጠናከር፤ የአገልግሎት አሠጣጥ ቅልጥፍና የመጨመር፤ በየጊዜዉ የተለዩት ደግሞ በዝርዝር አሠራር ሥርዓት እየተፈተሹ መንስዔዉ ታዉቆ ዘላቂ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎችን ተቋማት እንዲወስዱ ይደረጋል:: የሕዝብ እርካታ ከማሳደግ አንጻርም ያለዉ ፋይዳ ከፍተኛ ስለሆነ፤ የክትትል ዉጤቱም በየወቅቱ ለህዝብ ይፋ በማድረግ፤ ለቀረበዉ ጥቆማ የተወሰደዉን እርምጃ ግብረ-መልስ የመስጠት ሥራ እንደሚጠናከር በሪፖርቱ ተገልጿል::

**የ2015 በጀት አመት አስቸኳይ ሙስና መከላከል ተግባራት**

| ተ.ቁ | ፌደራል/ክልል | የጥናት ብዛት | በብር | መሬት ( በካ.ሜ) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፌደራል(25 ዘርፍ) | 820 | 1,318,754,267.48 | _ _ |
| 2 | ቤኒሻጉል ጉሙዝ | 31 | 39,378,291.20 | 99,038 |
| 3 | አማራ | 16 | 7,257,269.08 | 56,900 |
| 4 | ሲዳማ | 29 | 33,479,416 | 76,338 |
| 5 | ሐረሪ | 7 | 144,455,877.62 | 250 |
| 6 | አዲስ አበባ | 450 | 1,926,436,720.55 | 240,681.00 |
| 7 | ደ/ም/ኢትዮጵያ | 162 | 31,200,171.54 | 621,288 |
| 8 | ሶማሌ | - | 18,000,000.00 | 130,000 |
| 9 | ደቡብ/ብ/ብ | 18 | 777,729,015.05 | 289,482 |
| 10 | ኦሮሚያ | 120 | 139,089. | 1122 |
| ድምር | | 138 | 4,296,830,117.52 | 1,515,099 |

የፌደራል ክልሎች፣ከተማ አስተዳደር አፈጻፀም

# የሙስና መረጃ ቅበላ፣ ትንተና እና ተደራሽነት

ኮሚሽኑ የሙስና ወንጀል ምርመራ በራሱ የሚያከናዉን ቢሆንም፤ መረጃ-መር የሙስና መከላከል ስራዎችን ለማከናወንና የትዉልድ ሥነምግባር ግንባታ ችግር-ፈቺ ለማድረግ ከዜጎች የሚቀርበዉን ጥቆማ ቅበላ፤ መረጃ ትንተና እና የምርመራ ሥራ ተልዕኮ ለተሰጠዉ አካል የማቅረብ ሥራ ትኩረት በማድረግ እየሰራ ይገኛል:: ዜጎች የሙስና መረጃ ጥቆማ ለማቅረብ ተጨማሪ ወጪ እንዳያወጡ እና ለእንግልት እንዳይዳረጉ ከዚህ በፊት ውስን የመረጃ ጥቆማ አማራጮችን በማስፋት፤ በርካታ ጥቆማዎችን በበጀት ዓመቱ መቀበል ችሏል:: የዚህ ተግባር አፈጻጸም የሚለካዉም የቀረበዉን ሙስና መረጃ ጥቆማ ተንትኖ ለተገቢዉ ዓላማ የማዋል ምጣኔ ነው:: ከዚህ አንጻር፤ በበጀት ዓመቱ 803 የሚሆኑ የሙስና ወንጀል ጭብጥ ያመላከታሉ የተባሉ መረጃዎች የቀረቡ ሲሆን፤ ተጨማሪ የማጣራት ሥራዎች፤ ትንተናዎች እና ለባለድርሻ አካላት የመላክ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ መከናወኑን ሪፖርቱ ያሳያል::

ዜጎች በአካል፤ በስልክ፤ በጥሪ ማዕከል (988)፤ በኤ-ሜይል፤ በቴልግራም እና አዲስ በለማዉ የዲጂታል ጥቆማ ፖርታል አማካኝነት ጥቆማ ማቅረብ ችለዋል:: ይኸዉ የጥቆማ ዉጤት ከብሔራዊ ፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጥቆማ ዉጪ ነዉ:: በተጨማሪም የሙስና መረጃ ጠቋሚዎች የምክርና የከለላ ክትትል ማዕከል ማደራጀትና አሠራር ሥርዓት መመሪያ ተዘጋጅቷል:: የሙስና ወንጀል መረጃ ጥቆማ ከሰዉ ንክኪ ነጻ ሆነዉ፤ ዜጎች ተጨማሪ ወጪ ሳያወጡ፤ መረጃና ማስረጃም ጭምር እንዲያቀርቡ የሚያስችል የዲጂታል ፖርታል (https://epfs.gov.et) በማበልጸግ ሥራ ላይ ማዋል ተችሏል:: ለህዝብም በሚዲያ አማካኝነት የአጠቃቀም ሁኔታ ግንዛቤ እየተፈጠረ ይገኛል::

ኮሚሽኑ የብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አባል በመሆኑ፤ ከቀረቡ ጥቆማዎች አግባብነት ያላቸዉን በመምረጥ ለኮሚቴዉ አቅርቧል:: በቀጣይ የአፈጻጸም ሪፖርት ከሚመለከተዉ ባለድርሻ አካል ክትትል በማድረግ እና በመቀበል ብሔራዊ የሙስና መከላከል እና ቅነሳ ምጣኔ አገራዊ መረጃ ለማደራጀት ጥረት ያደርጋል::

# የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ

የመንግሥት እና የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላት እንዲሁም አግባብነት ያላቸዉ የተቋማት ሰራተኞች ሀብት እንዲያሳዉቁና እንዲያስመዘግቡ ክትትል የማድረግ፤ በምዝገባ መረጃዉ ትክክለኛ ስለመሆኑ የማረጋገጥ እና አግባብነት ያላቸዉ የመረጃ ግድፈቶች እንዲመረመሩ እና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ የማድረግ ተግባራት በአገርዓቀፍ ደረጃ በስፋት መከናወኑን ከሪፖርቶች ማየት ተችሏል:: ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት የነበረዉ የወረቀት ላይ የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ፤ የመረጃ ጥራት እና ተገቢነት ችግር ያለበት፤ ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ፤ ለተመዝጋቢዎችም አመቺ ያልሆነ እና የዉሳኔ ምክረ-ሐሳብ ለማመንጨትም አዳጋች የሆነ እንዲሁም የቅጽ ማከማቻ ቦታ በርካታ ቢሮዎችን የሚይዝ በመሆኑ ወደ ዲጂታል ማሳወቂያና ምዝገባ አሠራር ሥርዓት ቀይሯል:: የዲጂታል አሰራር ሥርዓት (https://dars.gov.et Dissclosure of Asset Registration System-DARS) በሌሎች አገሮች መልካም ዉጤት ያስገኘ በመሆኑ፤ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ምቹ በመሆኑ ለትግበራዉ ተገቢዉ ትኩረት ተሰጥቷል::

በበጀት ዓመቱ፤ የዲጂታል አሠራር ስርዓትን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ከማድረግ በፊት የሙከራ ሥራዎችን የማጠናቀቅ፤ የመረጃ አያያዝ ደህንነት ሥራዎችን የማጠናከር፤ ከሚመከለታቸዉ ባለድርሻ ተቋማት ጋር የመቀናጀት ሥራዎች ሲሰሩ ቆይቷል:: በተጨማሪም፤ ከዚህ በፊት የተመዘገቡት ሰነዶችን ወደ ዲጂታል የመቀየር ሥራዎች እና ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ሥራዎች በስፋት ተሰርቷል:: የቀድሞ የሰነድ ሀብት ምዝገባ (በቁጥር 750 ሺህ) ወደ ዲጂታል (306 ሺህ) አሠራር ሥርዓት የማሳደግ ሥራ ተሰርቷል:: በተጨማሪም 463 የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ አመራሮችን እና ተመራጮች የዲጂታል ሀብት ምዝገባ አካሂደዋል::

እንዲሁም ክልል/ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖችንም በማገዝ ወደ ደጂታል አሠራር ሥርዓት እንዲሸጋገሩ ድጋፍ እና ክትትል ተደርጓል:: የሥራ ክፍሉ የሥራ ስታንደርድና መመሪያ እንዲኖርም ረቂቁን በማዘጋጀት ለህግ ክፍል ቀርቦ የተሰጠው አስተያየት ተካቶ ለማጸደቅ በሂደት ላይ ነው:: የፌዴራል የመንግሥት ተቋማት፤ የልማት ድርጅቶች ውስጥ ለሚገኙ 80 የሙስና መረጃ ባለሙያዎች የግንዛቤ ስልጠና ተሰጥቷል:: የሀብት ምዝገባ መረጃን ተደራሽ ከማድረግና ሥልጠና ከመስጠት አንፃር፤ 393 መረጃዎች ለጠየቁው መንግሥታዊ አካል ተደራሽ የተደረገ ሲሆን ለ365 ባለሙያዎች በዲጂታል ሀብት ምዝገባ አሠራር ሥርዓት እና አጠቃቀም ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል::

የሀብት ምዝገባ መረጃ ማጭበርብርን በተመለከተ የጥቆማ ቅበላ ማበረታቻ ግንዛቤ በሚዲያ ማስተላለፍ ተችሏል:: ከዚህ በተጨማሪ የሙስና መረጃ ጠቋሚዎች የምክርና የከለላ ጥያቄዎችን ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እና መከታተል ተችሏል፤ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አሰራር ሥርዓት፤ የተመዝጋቢዎችን የግልጽነት እና የተጠያቂነት ደረጃ በማሳደግ ለጸረ-ሙስና ትግል የሚያስገኘዉ ፋይዳ ከፍተኛ ነዉ:: በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፤ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ በቂ የህግ ማዕቀፍ የተዘጋጀለት፤ ጠንካራ የዉስጥ አሰራር የተበጀለት እና




የመረጃ-መር ሙስና መከላከል ስራ ለማሳለጥ የላቀ ሚና እንደሚኖረዉ የታመነበት ነው::

ኮሚሽኑ ወደ ደጂታል ሥርዓት መሻገሩ እና መንግስትም የመረጃ ደህንነት ጥበቃ እንዲደረግ ለሚመለከታቸዉ ተቋማት ኃላፊነት መስጠቱ ከመቼዉም ጊዜ በላይ አበረታች ተግባር የተከናወነበት በጀት ዓመት ነዉ ማለት ይቻላል:: በቀጣይ በጀት ዓመት፤ የዲጂታል አሠራር ሥርዓት ቀሪ ሥራዎች ሲጠናቀቁ የምዝገባ ሽፋን የተሟላ በማድረግ፤ የመረጃ ትክክለኛነትን የማጣራት ሥራ ልዩ ትኩረት ይሰጣል:: ከፍትህ ዘርፉ ያለዉ የምርመራ እና ክስ ሂደቱን የማጠናከር ሥራዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ኮሚሽኑ ለሙስና መከላከል አጋዥ የሆኑ የመረጃ ማጥራት ስራዎችን እያከናወነ ለዉሳኔ ሰጪ አካላት የማቅረቡን ሥራ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል::

# የክልሎች የሃብት ምዝጋባ አፈጻፀም

| ተ.ቁ | የሀብት መዝጋቢ አካል | ሀብታቸውን ያስመዘገቡ አመራሮችና ባለሙያዎች | | | ሀብታቸውን ያስመዘገቡ ከፍተኛ አመራሮችና ተሿሚዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድምር | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | የፌዴራል ተቋማት በ25 ዘርፎች የተመዘገበ | 84,476 | 60,810 | 147,286 | 458 | 5 | 463 |
| 2 | ክክልሎች | 46,563 | 23,886 | 70,449 | 2,764 | 920 | 3,684 |
| | ጠቅላላድምር | 131,039 | 84,696 | 215,735 | 3,222 | 925 | 4,147 |

# የሀብት ምዝገባ መረጃ የማጣራትና የጥቅም ግጭት መከላከል

የሀብት ምንጭ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ እና የጥቅም ግጭትን የመለየቱን ስራ አስመልክቶ በበጀት ዓመቱ በአራት ዙር መከናወኑን ሪፖርቱ አመላክቷል:: በዚሁ መሰረት በመጀመሪያው ዙር ከተለያዩ ዘርፎች የ53 ሀብት አስመዝጋቢዎችና የ74 ቤተሰቦቻቸውን በድምሩ የ127 ግለሰቦችን የሀብት ምንጭ የማጣራትና የጥቅም ግጭት የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን፤ በሁለተኛው ዙር ከስምንት ዘርፎች ከተማና መሠረተ ልማት፣ ትራንስፖረትና ሎጂስትክስ፣ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ዘርፍ፣ ግብርና ዘርፍ፣ ትምህርት፣ገንዘብ፣ ማዕድን፣ ከተማ እና መሠረተ ልማት እና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ስር ሀብታቸውን ያስመዘገቡ የ56 ሀብት አስመዝጋቢዎችና የ128 ቤተሰቦቻቸውን በድምሩ የ184 ግለሰቦችን የሀብት ምንጭ የማጣራትና የጥቅም ግጭት የመለየት ሥራ ማከናወን ተችሏል::

በሶስተኛው ዙር ከተለያዩ ዘርፎች የ16 ሀብት አስመዝጋቢዎችና የ37 ቤተሰቦቻቸውን በድምሩ የ53 ግለሰቦችን የሀብት ምንጭ የማጣራትና የጥቅም ግጭት የመለየት ሥራ ተከናዉኗል:: በአራተኛው ዙር ከአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና ከገቢዎች ዘርፍ ጥቆማ የቀረበባቸው 26 አመራሮች እና 67 ቤተሰቦቻቸው በድምሩ 93 ግለሰቦችን የሀብት ምንጭ የማጣራትና የጥቅም ግጭት የመለየት በድምሩ የ151 አመራሮችን እና የ306 ቤተሰቦቻቸው በአጠቃላይ የ457 ግለሰቦችን የሀብት ምንጭ ማጣራት እና የጥቅም ግጭት የመለየት ስራዎች ተሰርተዋል:: በበጀት ዓመቱ የ17 ተመዝጋቢዎች የመረጃ ማጣራት ግኝት ለምርመራ የተላከ ሲሆን ሌሎች የመረጃ ማጣራት ግኝቶች በመለየት ላይ ይገኛሉ:: ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ምርመራ እንዲካሄድና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ መረጃ የማቅረብ ሥራ በታቀደው መሰረት ማከናወን ተችሏል::

ሌላው በተመረጡ 3 ዘርፎችና በሥራቸዉ ባሉት ተቋማት (አሰራር ሥርዓት) የዉሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እና የጥቅም ግጭት ሥጋት ለመከላከል ጥናት በማድረግ ሪፖርት ማዘጋጀት ተችሏል:: የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ዉጤታማነት የሚረጋገጠዉ በዋናነት የሀብት ምንጭ መረጃ በተገቢዉ ተጣርቶ፤ ተመዝጋቢዉ ትክክለኛ መረጃ መስጠቱና ኮሚሽናችን ከሶስተኛ ወገን መረጃ ሰብስቦ በማመሳከር በሚያገኘዉ መሰረት ግልጽነት እና ተጠያቂነት በመፍጠር ነው:: የኮሚሽኑ የሶስተኛ ወገን መረጃ የማጣራት ሂደት የሚያመላክተው በአንድ በኩል ለተመዝጋቢዉ የግልጽነት ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፤ በሌላ መንገድ ደግሞ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ከምችት ከተገኘም ለኮሚሽኑ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ነው::

ኮሚሽኑ በዚህ አሠራር ስርዓት በቀጣይ የመረጃ ማጣራት ሥራዉ ጥራት እንዲኖረዉ፤ በየዘርፉ ያሉ ከፍተኛ አመራሮች እና አግባብነት ያላቸዉ ሌሎች ተመዝጋቢዎች እንዲካተቱ እዲሁም የተጠያቂነት ምጣኔ በፍትህ ዘርፉ በኩል ዉጤታማ እንዲሆን ክትትል የማድረግ ሥራዎች በትኩረት ይሰራል:: በዚህ በጀት ዓመት፤ የሀብት ምዝገባ ላይ ትኩረት ተደርጎ ከሚሰራበት ወደ ሀብት መረጃ የማጣራት ሥራ ትኩረት እንዲደረግ የአሠራር ሥርዓት እና የአዲስ አደረጃጀት ማሻሻያዎች ሥራ ላይ ዉሏል::

# የሙስና ወንጀል ምርመራ እና ክስ ተግባራት

**ውሳኔ በተሰጠባቸው 539 የሙስና ወንጀል መዝገቦች 8,840,600 ብር ቅጣት ተጥሏል**

በፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት ባለፈው በጀት አመት ውስጥ በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ እጅ የነበሩ የሙስና ወንጀል ምርመራ መዛግብት ብዛት 350 ከባድ እንዲሁም 278 ቀላል በድምሩ 628 ሲሆኑ ዓቃቤ ሕግ የዘጋው የምርመራ መዛግብት ብዛት 127 መሆኑን መረጃው ያሳያል:: በበጀት አመቱ ተከሣሽን ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት የተቋረጡ የምርመራ መዝገቦች ብዛት የሌሉ ሲሆን ዓቃቤ ሕግ ክስ የመሰረተባቸው ምርመራ መዝገቦች ብዛት 114 ከባድ እና 75 ቀላል በድምሩ 189 ናቸው:: እንዚህ መዝገቦች ሙሉ በሙሉ ክስ በመመስረት ወጪ ሆነው ወደ ፍርድቤት የተላኩና የተከፈቱ መዝገቦች ናቸው::

ከፖሊስ ከመጡት የምርመራ መዝገቦች መካከል በ38/ሐ/ መሠረት ለተጨማሪ ምርመራ ተብለው ለፖሊስ የተመለሱ የምርመራ መዝገቦች ብዛት 169 መሆናቸውን እና ስልጣኑ ወደ ሆነ አካል የተላለፈ ደግሞ 54 የምርመራ መዝገቦች መሆናቸውን መረጃው ያሳያል:: በጠቅላላው በበበጀት ዓመቱ ውስጥ አቃቤ ህግ የተለያዩ ውሳኔ የሰጠባቸው የምርመራ መዛግብት ብዛት 319 ከባድ እና 220 ቀላል በድምሩ 539 መዝገቦች ናቸው:: ውሳኔ በተሰጠባቸው መዛግብት በገንዘብ ቅጣት የተወሰነባቸው ጠቅላላ ገንዘብ ብዛት 8,840,600 ብር ነው:: በዚሁ መሰረት የሁሉም መዝገቦች አማካይ የምርመራ መዘገብ የማጥራት ምጣኔ /Clearance Rate/ በመቶኛ 86% መሆኑን መረዳት ተችሏል::

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ርዕሰ -አንቀፅ

## የፀረ-ሙስና ትግል የሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ባለቤትነት የሚጠይቅ ነው!

ኢትዮጵያን ከድህነትና ከኋላቀርነት የማላቀቅ እንዲሁም የዜጎቿን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ የመለወጡ ሂደት ሙስና በተንሰራፋበት ሁኔታ ውስጥ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በመንግስት የሚካሄደው የልማት እና የለውጥ ጥረት ከማፋጠን ጎን ለጎን ሙስናን በተቀናጀ ሁኔታ የመከላከልና የመዋጋት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ካልቀጠለ ለልማት የሚመደበው ሀብት ለታለመለት ዓላማ ስለማይውል ከታሰበው ግብ ሊደረስ አይቻልም፡፡ የዜጎች የኑሮ መሻሻልም ሆነ የአገር ዕድገት ከቃላት ባሻገር እውን ሊሆኑ አይችሉም፡፡

መልካም ሥነምግባርን በዜጐች ዘንድ በማስፋፋት እና በማስረጽ፣ የሙስና መከላከል ተግባራትን በማጠናከር ሙስና በልማት እና እድገት ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ መግታት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ወቅታዊ ተግባር ነው፡፡ የፀረ-ሙስና ትግሉ የአንድ ወይም የተወሰኑ አካላት ኃላፊነት ብቻ ባለመሆኑ ሁሉም የሕብረተሰብ አካል ባለቤት ሊሆን ይገባል፡፡

ኮሚሽኑ በበጀት አመቱ ሙስና የሚያስከትለውን አደጋ ከጅምሩ ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የሪፎርም ስራዎችን ቀይሶ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከተወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች መካከልም በአገር አቀፍ ደረጃ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል እና ለመዋጋት ዘርፍ ተኮር የአሰራር ስርዓትን በመተግበር ቅንጅታዊ አሰራርን የተከተለበት መንገድ ተጠቃሽ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ ብሔራዊ የሥነ ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ፖሊሲ ዝግጅት፣ የከፍተኛ መንግስት ኃላፊዎች የጥቅም ግጭት መከላከል ደንብ ዝግጅት እና ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ጥናቶች በጉልህ ይጠቀሳሉ፡፡

በሌላ በኩል በአገራችን የሚካሄደውን የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚካሄደው የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ጋር ለማስተሳሰር እና ጠቃሚ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ የሚረዳ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የኮሚሽኑ አመራሮች በተለያዩ አህጉር እና አለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመሳተፍ የሀገራችንን የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ለሌሎች ሀገራት ማጋራት ተችሏል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከሌሎች ሀገራት ጠቃሚ የሆኑ ልምዶችን በማምጣት የማሻሻያ ትግበራዎችን በየጊዜው ሲተገብር ቆይቷል፡፡

እስካሁን ድረስ በኮሚሽኑ የተደረጉ ጥረቶች ሙስና በአገራችን የልማት እንቅስቃሴ ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ ለማድረስ እንዳይችል አስተዋጽኦ ቢያበረክትም ሙስና የሚያደርሰው አደጋ ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ባሳለፍነው የበጀት ዓመት ያለው የዓለም አቀፍ እንዲሁም የሀገራችን ተሞክሮ የሚያሳየው ሙስና ከዋና ዋናዎቹ የዓለማችን ችግሮች መካከል ጉልህ ሆኖ የሚጠቀስ መሆኑን ነው፡፡ በኢትዮጵያም ችግሩ የልማትና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅስቃሴዎችን በማደናቀፍ ብሔራዊ ስጋት ተብሎ የታወጀበት ወቅት ላይ በመሆኑ በጥንቃቄ እና በትኩረት ካልተያዘ ለሚታሰበው ልማት እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አልፎ ተርፎ ለሰላማችን እንቅፋት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ዜጋ ሙስናና ብልሹ አሰራር ከብሔራዊ ስጋት አልፎ ሙሉ በሙሉ ሰላማችንን ማሳጣት ደረጃ ላይ ሳይደርስ በቁርጠኝነት ለማስወገድ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፡፡

# በበጀት አመቱ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተከናወኑ የሪፎርም ተግባራት

## የነዳጅ ግብይት ዲጂታል ሪፎርም ያስገኛቸው ውጤቶች

መንግስት ከጀመራቸው የሪፎርም ተግባራት መካከል ባሳለፍነው በጀት ዓመት መጨረሻ አካባቢ ወደ ትግበራ የገባው የነዳጅ ግብይትን በዲጂታል አማራጭ የማስፈፀም ሪፎርም በጉልህ ይጠቀሳል፡፡ በሪፎርሙ መሰረት ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ እንዲሁም ከሰኔ ወር ጀምሮ በሁሉም ክልሎች የነዳጅ ግብይቱ በዲጂታል አማራጭ እንዲካሄድ ተወስኖ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

ትግበራው ካስገኛቸው ውጤቶች አንዱና ዋናኛው በነዳጅ ሥርጭት እየታየ ያለውን ብክነት፤ ህገ-ወጥነትና ኮንትሮባንድ በማስወገድ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ማድረግ አመረቂ ውጤቱ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጎረቤት አገሮች ጋር በእጅጉ የተቀራረበ የችርቻሮ ዋጋ እንዲኖረ በማድረግ ቀደም ሲል በህገ ወጥ መንገድ በገፍ ወደ ውጭ የሚወጣው ነዳጅም በከፍተኛ መጠን እየቀነሰ መምጣት መቻሉን ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ሌላው ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የነዳጅ ድጎማ በማድረግ በታሪፍ አማካይነት ጥቅሙን ለህብረተሰቡ በማስተላለፍ ከሐምሌ 2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 10/2015 ብር 15.15 ቢሊዮን ክፍያ እንዲፈፀም መደረጉ በአጠቃላይ የነዳጅ ድጎማን ሙሉ በሙሉ በማስቀረት ወደ ቀደመው የዋጋ ማረጋጊያ አስተዳደር ሥርዓት ለመመለስ የሚያስችል አስተማማኝ ሁኔታ መፈጠር ተችሏል፡፡

ከዚህ አንጻር ዲጂታል የነዳጅ ግብይት ትግበራ ፍትሀዊነትን የማረጋገጥና ሕጋዊነትን የማስፈን ውሳኔ መሆኑን መረዳት አያዳግትም። በተለምዶው አሰራር በተለያዩ ክልሎች ሕገ ወጥ የነዳጅ ንግድ በስፋት ሲካሄድ የቆየ ሲሆን ከነዚህ ሕገ ወጥ ተግባራት መካከል ነዳጅን ከማደያ ውጪ በህገወጥ መንገድ መቸርቸር፣ መንግስት ከተመነው ታሪፍ በላይ ዋጋ ጨምሮ መሸጥ፣ ነዳጅ ማደያ ውስጥ እያለ የለም ብሎ እጥረት በመፍጠር ህብረተሰቡን የማጉላላትና ኢኮኖሚያዊ ጫና ማሳደር በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህንና መሰል ተግባራትን ወጥነት ባለው መንገድ ለመቆጣጠር ዲጂታል የነዳጅ ግብይት ትግበራ መጀመሩን ባለስልጣኑ ሲያሳውቅ ቆይቷል፡፡

ግብይቱን በተመለከተም የተለያዩ አማራጮች ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የቴሌ ብር እና የንግድ ባንክ ሲቢኢ ብር እንዲሁም በሌሎች ባንኮች አማካይነት የክፍያ ስርዓት እየተሠራ ይገኛል፡፡ ይህ የሪፎርም ርምጃ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ አስተዋጽኦው የጎላ በመሆኑ በሌሎች ተቋማት መሰል ርምጃዎች እንዲወሰዱ ይጠበቃል፡፡



ወ/ሮ ሳህረላ አብዱላሂ፡ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ዋና ዳይክተር

## የትምህርት ጥራት እና የፈተና ማጭበርበርን ለማስቀረት የትምህት ዘርፉ ሪፎርም

ሙስና በሀገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የወንጀል አይነት ነው፡፡ ሀገራት ለእድገት የሚያደርጉትን ጉዞ በማቀጨጭና በማሽመድመድ ዜጎችን ለእንግልትና የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዳያገኙ ከማድረጉም ባሻገር ለሰላም ማጣትና ለስደት እንዲዳረጉ ከሚያደርጉ መንስኤዎች አንዱ እና ዋነኛው ነው። ሙስና በኢትዮጵያ አንዱ እና ትልቁ ችግር ሲሆን ይበልጥ ይህ ችግር ከሚንፀባረቅባቸው ዘርፎች መካከል የትምህርት ዘርፍ እንደሆነ ቀደም ሲል የተጠኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተለይ በትምህርት ሴክተር ላይ የሚፈጸም ሙስና በትምህርት መሳሪያዎችና አገልግሎቶች፣ በትምህርት ተደራሽነት፣ በትምህርት ፍትሃዊነትና ጥራት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት "በትምህርት ተቋማት ከመማር ማስተማር ጋር በተያያዘ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የትምህርት መረጃ አሰጣጥ፣ የማስፋፊያ ግንባታ፣ በግዥ፣ በጀት አጠቃቀምና መሰል ተግባራት ለሙስና ሊጋለጡ የሚችሉ የስራ አካባቢዎች እንደሆኑ ያሳያሉ፡፡ ከእነዚህ በትምህርት ላይ ከሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ሀሰተኛ የት/ት ማስረጃ መስፋፋት ነው፡፡

አሁን ላይ ለፍቶ ግሮ ተምሮ ውጤታማ መሆን የመሆን ጉዳይ እና በሀሰተኛ የትምህርት መረጃ ስራ የመግባት ሁኔታ የተምታታበት እንደሆነ መረጃዎች ያነሳሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሱት ደግሞ በሀሰተኛ የት/ት ማስረጃ የተቀጠሩ ሰዎችን ሞዴል ማድረግ ፣የሥራ አለመቀጠር፣ ህግና ስርዓትን ያልተከተሉ የቅጥር ሁኔታዎች መኖራቸው እና ተገቢ ያልሆነ እድገት ለማግኘት መፈለግ መሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በዘርፉ በርካታ የሪፎርም ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው የአስራ ሁለተኛ ክፍል መውጫ ፈተና በዩኒቨርስቲዎች በጥብቅ ዲሲፕሊን በማካሄድ ትክክለኛ እና ከኩረጃ ነጻ የሆነ ውጤት እንዲመዘገብ የተሄደበት ርቀት አንዱ ነው፡፡ ውጤቱ እንደ ሀገር የትምህርት ጥራቱ ያለበትን ክፍተት በከፍተኛ ሁኔታ ያመላከተ ቢሆንም በቀጣይ ችግሩን ለመቅረፍና መፍተሔዎችን ለማመንጨት እንደሚረዳ ግን ይታመናል፡፡ ተማሪዎችም ለፍተው እና ጥረው ውጤት እንዲያስመዘግቡ መነሳሳትን የሚፈጥርላቸው ይሆናል፡፡

ሌላው የዩኒቨርስቲ መውጫ ፈተና ሲሆን በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ ብቁ ትውልድ ለማፍራት የተወሰደ ወሳኝ ርምጃ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በመንግስትና በግል ተቋማት ሁለተኛ ድግሪ ለመማር የመግቢያ ፈተና ለመስጠት መታቀዱ በዘርፉ ቁርጠኛ አመራር መኖሩን አመላካች ነው፡፡

ኮሚሽኑ በበኩሉ በትምህረት ዘርፉ እየንተሰራፋ የመጣውን ሙስናና ብልሹ አሰራር በሚመለከት ጥናት አስጠንቶ ወደ ተግባር የገባ ሲሆን በዚሁ መሰረት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ለመስጠት እንዲያስችል «በትምህርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችና መከላከያ መንገዶቹ» በሚል ርዕስ ከባለድረሻ አካላት ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አካሂዷል፡፡ በዚህ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ ጥናት ቀርቦ ውይይት የተደረገ ሲሆን በጥናቱ እንደ ትልቅ የሙስና ስጋት ከተጠቀሱት ውስጥ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች መኖር አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ ይህን የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃን ለመከላከል የማጣራት ሥራ መጀመሩ ተከትሎ በተለያዩ ክልሎች በተለይም ደግሞ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃን የማጣራትና የመፈተሽ ስራ በሰፊው ተሰርቶ ውጤቶች ታይተዋል፡፡



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

## ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች ላይ የተወሰዱ ርምጃዎች

በጋምቤላ ክልል ሀሰተኛ ሰርተፍኬት በማሳተም ሕዝብና መንግሥትን የሚያጭበረብሩ አካላት መኖራቸው እንደተደረሰበትና ይህን ተከትሎ በተደረገ የማጣራት ሥራ 250 ሐሰተኛ ሰርተፍኬትን የሚጠቀሙ አካላት መገኘታቸውንና ይህን ድርጊት የሚፈጸሙትን በሕግ አግባብ ተጠያቂ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በሌላ በኩል የተለያዩ የመንግስት እና በግል ኮሌጆች/ ዩኒቨርሲቲዎች ሳይማሩ ሀሰተኛ የትምህርት ማሰረጃ መጠቀም ወይም ያገኙትን ውጤት በህገወጥ መንገድ ማሳደግ እየተለመደ የመጣ ጉዳይ ሲሆን ከዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በ2015 የቀረቡለትን የትምህርት ማስረጃ ማጣራት ጥያቄዎችን ተከትሎ ባደረገው የማጣራት ሥራ 250 ሕጋዊነት የሌላቸው ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች ማግኘቱን አስታውቋል። ዩንቨርስቲው ምሩቃን በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ተቋማት በሚቀጠሩበት ወይም ተቀጥረው እየሠሩ ባሉበት ጊዜ የሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃ ትክክለኛነት ይጣራልን ጥያቄዎችን እየተቀበለ የትምህርት ማስረጃ አጣርቶ በማረጋገጥ በተከታታይ ምላሽ በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ገልጿል።

በተመሳሳይ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ማጣራት እንዲደረግባቸው በተለያዩ ተቋማት ከቀረቡለት የትምህርት ማስረጃዎች ውስጥ እስካሁን 21 ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች የተገኙ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ተቋማት የግለሰቦች የትምህርት ማስረጃ ተገቢነት ተጣርቶ እና ተረጋግጦ እንዲገለጽ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በ42 የትምህርት ማስረጃዎች ላይ በሁለት ዙር ባካሄደው የህጋዊነት ማረጋገጫ ሥራ 21ዱ ሐሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር አሳውቋል። ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃው በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ስም ተጭበርብሮ በተሰራ ማሕተም፣ በአመራር የስምና የማዕረግ ቲተር እንዲሁም በሐሰተኛ ፊርማ ተመሳስሎ የተሠራ መሆኑ ተመላክቷል።

ግለሰቦቹ ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመጠቀም በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ተቀጥረው በመስራት የማይገባቸውን ጥቅም እያገኙ መሆኑም ተገልጿል። ዩኒቨርሲቲው የሐሰተኛ ትምህርት አጣሪ ግብረ ኃይል አቋቁሞ ሰፊ የማጣራት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልጿል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ተገኝቶባቸዋል ያላቸውን አመራሮች እና ባለሙያዎች ላይ እርምጃ ወስዷል። ክልሉ 24 ሺ ከሚጠጉ ሠራተኞች ሠነድ ወደ 2 ሺህ 241 ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የያዙ ሠራተኞችና አመራሮች ተገኝተዋል። ከዚህም ውስጥ ከፋ ዞን በመንግስት መስሪያ ቤቶች እስካሁን በተደረገ ፍተሻ ከአምስት መቶ ሀያ በላይ በሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተቀጠሩ ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች ላይ እርምጃ መወሰዱ ተገልጿል። በሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በየመንግስት መስሪያ ቤት የሚገኙ አካላት የመንግስትን ሃብት ከማባከን ባሻገር ባልተማሩበት ሙያ በሃሰት ማስረጃ ህዝቡ ትክክለኛ አገልግሎት እንዳያገኝ ሲያደርጉ ነበርና ከስራ እና ከደሞዝ ከመታገድ ባሻገር በህግ የመጠየቅ ርምጃም ሲወስድ ቆይቷል።

በደቡብ ክልል ደግሞ ከ17 ሺሕ በላይ የትምህርት ማስረጃዎች ላይ በተደረገው የማጣራት ሥራ 1ሺሕ 131 ማስረጃዎች ሀሰተኛ ሆነው መገኘታቸውን የተገለፀበት አመት ነበር። ቢሮው በ2015 ዓ.ም በክልሉ 5 ሺህ 672 የብቃት ማረጋገጫ ላይ በተደረገ ፍተሻ 767 የብቃት ማረጋገጫዎች ሀሰተኛ ሆነው ተገኝተዋል። በተቋማት ከ23 ሺሕ በላይ መዝገቦች ላይ ፍተሻ በማድረግ ከ4 ሺሕ በላይ ቅጥር፣ ዝውውር እና የደረጃ እድገት በሕገ ወጥ መልኩ በመፈፀሙ ከ2 ሺሕ በላይ አመራሮች እና ባለሙያዎችን ተጠያቂ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ ውስጥ ከ144 በላይ አመራሮችን ከኃላፊነት ማንሳት መቻሉ ክልሉ አስታውቋል።

በዚህም መሰረት የማጣራት ሂደት ከአንዳንድ ተቋማት የቀረቡ የዩኒቨርሲቲው ምሩቃን የትምህርት ማስረጃዎች፤ በዩኒቨርሲቲው በተሰጣቸው የተማሪ ውጤት ኮፒ ላይ የአጠቃላይ ነጥብ ለውጥ የተደረገባቸው እንዲሁም ፈጽሞ በዩኒቨርሲቲው ያልተማሩባቸው ሐሰተኛ ዲግሪ ማስረጃዎች መሆናቸውን ማረጋገጡን አስታውቋል።

በመሆኑም መሰል ኃላፊነት የጎደላቸው ተግባራት እንዳይበረታቱ ብሎም ሕዝብና መንግሥት ሙያዊ ብቃት በሌላቸውና ኃላፊነት በጎደላቸው ዜጎች ለጉዳት እንዳይጋለጥ በማሰብ በዩኒቨርሲቲው የትምህርት ማስረጃ ላይ የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ በማስመሰልና በመቀየር እንዲሁም፤ በዩኒቨርሲቲው ሥምና ሎጎ ያልተማሩበትን ዲግሪ ይዘው የማጭበርበር ተግባር ላይ የተሠማሩና ወደ ፊትም የሚሠማሩ ቢኖሩ ለሕዝብ የማጋለጥ ሥራ በተከታታይነት እንዲሠራ ዩኒቨርሲቲው መወሰኑን ገልጿል።

በበጀት ዓመቱ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት 18 ሺህ የትምህርት ማስረጃዎች ትክክለኛነት ተፈትሾ 921 (አምስት በመቶዎቹ) ህገ-ወጥ ሆነው እንዳገኛቸው ትምህርት ሚንስቴር አስታውቋል። ቀጣሪ ተቋማት ለሚኒስቴሩ ይረጋገጥልን ብለው ባቀረቡት ጥያቄ ደግሞ 225 የትምህርት ማስረጃዎች ተመርምረው 40 በመቶዎቹ ሀሰተኛ ሆነው መገኘታቸውንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

በመሆኑም እንደ ሀገር ፈተና የሆነውን የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ከምንጩ ለማድረቅ በቅንጅት እየተሰራ መሆኑንና የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የማጠራት ዘመቻ በጥቆማ እና ሰዎችን በማጋለጥ ውጤት ተገኝቶበታል ማለት ይቻላል። ነገር ግን አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። የትምህርት መዋቅሩ በሥነምግባር የታነፀ ትውልድን መገንባት ዋነኛ አላማው በመሆኑ የተማሪዎች የሥነምግባር ጉዳይን ሁሌም ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት አለበት።

በስነምግባር የታነጸ ትውልድን ለመገንባት የትምህርት መዋቅሩ ሚናውን እንዲወጣ በአዲሱ ስርአተ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል። ተማሪዎች ስነምግባራቸውን ገንብተን ብልሹ አሰራሮች በማክሰም የራሳችንን ኃላፊነት መወጣት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ከሌሎች ዘርፎች በተለየ ሁኔታ በትውልድ ላይ የሚሰራ እንደመሆኑ ዘርፉ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በትምህርት ዘርፍ ላይ ሙስናና ብልሹ አሰራር ሲከሰት ኪሳራው ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ጭምር ነው። ስለሆነም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዘሳቤ ማሰጨበጫ ስራዎች በተከታታይነት መስራት ያስፈልጋል። በዘርፉ በሚሰሩ የግንዛቤ ማስጨበጫና የምክክር ስራዎች የሚነሱ የመፍትሔ አመራጮች ተግባራዊ እንዲሆኑ በዘርፉ ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲቀንስ ባለድርሻ አካላት በሁለንተናዊ ትብብርና ቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

# የመንግስት የግዥ ስርዓትን ወደ ኤሌክትሮኒክስ ሲስተም መቀየር ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመቅረፍ ያለው ፋይዳ

የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ብልሹ የግዥ ስርዓትን በመቅረፍ የመንግስት በጀት በታለመለት አገልግሎት እንዲውል በማድረግ የሀገርን ስልጣኔ ከማምጣት ባሻገር ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዳይፈጠር ያግዛል፡፡ በሃገር አቀፍ ደረጃ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ከታቀዱት ከአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ስትራቴጂክ ግቦች አንዱ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ነው፡፡ ኤሌክትሮኒክ የመንግስት የግዥ ስርዓት በግዥ ሂደቱ እየተፈጠሩ ያሉትን የአሰራር ችግሮች መቅረፍ የሚችል እና በአንዳንድ የራሳቸው ጥቅም ፈላጊ አካላት ለውስን ተጫራቾች ብቻ ታስቦ የሚዘጋጀውን የተጭበረበረ የጨረታ ሰነድ በማስቀረት ህጋዊና ህገወጥ የሆነውን ለመለየት የሚያስችል ሲስተም ነው፡፡

ሙስና በሀገሪቱ ባህል እየሆነ በመጣበት ሁኔታ እና ግልፅኝነትና ተጠያቂነት ባልሰፈነበት በዚህ ጊዜ ኤሌክትሮኒክ የመንግስት የግዥ ስርዓት የደረሰበት ደረጃ የሚያበረታታ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ሲፈፀም የነበረውን ማንዋል የግዥ ስርዓት ማዘመንና ወደ ዲጂታል የግዥ ስርዓት መቀየር እንዲሁም የተቀላጠፈና የወጭ ብክነትን መቀነስ የሚያስችል የግዥ ስርዓትን የሚፈጥረው ይህ የኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓትም በአማካይ ከ217 ቀናት ወደ 30 ቀናት በመቀነስ በበፊቱ ግዥ ሥርዓት የነበረውን የጊዜ መጓተት የሚያሳጥር እና ሰፊ ተደራሽነትን በመፍጠር፣ አስተዳደራዊ ወጪዎችን በመቀነስ፣ ውድድርህን በማስፋት ከሰዎች ጋር የሚደረግን ግንኙነት በመቀነስ በዘርፉ የነበረውን የመልካም አስተዳደርና የሙስና ችግርን መቀነስ እንደሚያስችል የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን መረጃ ያሳይል፡፡

አንድ የመንግስት ተቋም ከወረቀት ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዥ በመግባት ማንኛውንም ግዥ ሲፈፅም የበጀቱን 5 እስከ 25 በመቶ ያተርፋል፡፡ በቀላሉ

የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (e-GP)

5 በመቶ የሚሆን ወጪን ቢቆጠብ 40 ሚሊዮን ብር እንዲቆጥብ ያደርገዋል፡፡ ከመንግስት ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከ60 እስከ 70 በመቶ የሚሆነው በጀት ለግዥ የሚውል በመሆኑ በጀቱ ለታለመለት አላማ እንዲውል በኤሌክትሮኒክስ ግዥ መፈጸም አስፈላጊ ነው። ከ2019 ዓ.ም ጀምሮ በሙከራ ደረጃ በ9 ተቋማት ላይ ሲሰራ የነበረው የኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ስርዓት አሁን ላይ 63 ተቋማትን በመጨመር የሙከራና የትግበራ ስራ እየተሰራ ሲሆን በጥቂት ወራት ውስጥም ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ እንደሚገባ ተገልጧል፡፡



## በ2015 በጀት አመት የኮሚሽኑ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ተሳትፎዎች



ክቡር ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙዔል ኡርቃቶ ለ6ኛ ዙር በተካሄደው ዓመታዊ የአፍሪካ አገሮች የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ጉባዔ በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ እየተካሄደ ባለው መድረክ ተሳትፈዋል፡፡



ም/ኮሚሽነር ወዶ አጦ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬሽን (UNCAC) አፈጻጸም ላይ በተካሄደ ስብሰባ ተካፍለዋል፡፡




የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በኡጋንዳ ኢንቴቤ የምሥራቅ አፍሪካ ልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ባዘጋጀው የፀረ-ሙስና ጥምረት ወርክሾፕ ተሳትፈዋል፡፡

በየትኛውም ቦታ ሆነው፣ በገጠርና በከተማ፣ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ሆነው በመንግሥት እና ሕዝብ ተቋማት እና በልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከኢትዮጵያ በሙስና የሸሹ ሀብቶችን መረጃና ማስረጃ ካገኙ ይጠቁሙ።



# በከባድ የሙስና ወንጀል የተከሰሱት የአዲስ አበባ እሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሰራተኞች ወደ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ታዘዘ



ከ40 ሚሊየን ብር በላይ የአልባሳት ግዢ ጋር ተያይዞ በከባድ የሙስና ወንጀል የተከሰሱ የአዲስ አበባ እሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሰራተኞች ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

ተጠርጣሪዎቹ በቀረበባቸው የሙስና ወንጀል ክስ የዋስትና መብት ጥያቄያቸው ውድቅ ተደርጎ ነው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ወደ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ የታዘዘው።

ተከሳሾቹ 1ኛ የአዲስ አበባ እሳት እና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽነር ሰለሞን ፍስሃ፣ 2ኛ የተቋሙ የመንግስት የግዢ ዳይሬክተር ግሩም ወልዴ፣ 3ኛ የኮሚሽኑ የለውጥ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ደረጀ ተፈራ፣ 4ኛ የኮሚሽኑ የሎጀስቲክስ ምዝገባና ቁጥጥር ባለሙያ ወንድሜነህ ምስጋናው፣ 5ኛ የአደጋ ስጋት ትግበራ ቡድን መሪ እዮብ ታደሰ ካሳ፣ 6ኛ በኮሚሽኑ የህክምና ባለሙያዋ ሲስተር አልማዝ ጌቶ፣ 7ኛ የአደጋ መረጃ ሀርድ ዌርና ሶፍትዌር ባለሙያ መስፍን ለገሰ እና 8ኛ ነጋዴ የሆኑት ንጉስ አማን የተባሉ ተከሳሾች ናቸው ።

ከእነዚህ ተከሳሾች መካከል 1ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች ፍርድ ቤት ያልቀረቡ ሲሆን፥ ቀሪ ተከሳሾች ቀርበዋል።

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ህግ በተከሳሾቹ ላይ የተሳትፎ ደረጃ ጠቅሶ ባቀረበው የከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ላይ እንደተመላከተው በሰኔ ወር በ2014 በጀት አመት ተከሳሾቹ የግዢ ጨረታ ሂደት ውስጥ በመሳተፍና በስውር በመመሳጠር ከባድ የሙስና ወንጀል መፈጸማቸው ነው የተገለጸው፡፡

በወቅቱ በተደረገ የገበያ ዳሰሳ ጥናት የአልባሳቱ ዋጋ 46 ሺህ 923 መሆኑ እየታወቀ ተከሳሹቹ ግን ብልዶዘር የተሰኘ የእሳት አደጋ መከላከያ ልብስን ከፍተኛ በሆነ ዋጋ ማለትም በፍሬ 184 ሺህ 644 ብር ከ8ኛ ተከሳሽ ተጫራች ድርጅት ግዢ እንዲፈጸም በማፅደቅ አጠቃላይ 217 ፍሬ አልባሳትን በ40 ሚሊየን 67ሺህ 748 ብር መግዛታቸው ተጠቅሷል፡፡

በዚህም በመንግስት ላይ በልዩነት 29 ሚሊየን 885ሺህ 441 ብር ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል ተብሎ በክስ ዝርዝሩ ላይ ተጠቅሶ ነበር።

ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸውና በችሎት ከተነበበላቸው በኋላ የዋስትና መብት ይከበርልን ጥያቄ አቅርበዋል።

ዐቃቤ ህግ በበኩሉ፥ የቀረበባቸው የከባድ ሙስና ክስ አንቀጹ ዋስትና እንደማያሰጥ ገልጾ ተከራክሯል።

ክርክሩን የመረመረው ፍርድ ቤቱ ዛሬ በዋለው የችሎት ቀጠሮ የዋስትና ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረግ ወደማረሚያ ቤት እንዲወርዱ አዟል።

ተከሳሾቹ ወንጀሉን አልፈጸምንም ሲሉ የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤህግ ምስክሮች እንዲሰሙለት ጠይቋል።

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ህግ ምስክሮችን ቃል ለመስማት ለጥቅምት 7 እና 8 ቀን 2016 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠቱን ፋና ዘግቧል።

# ሀሰተኛ ሰነዶችን በመገልገል ከ4 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ተከሳሽ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት ተቀጣ

በሀሰተኛ ማንነት የህዝባዊ ድርጅቶችን ሀሰተኛ ሰነዶችን በመገልገል ከ4 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ተከሳሽ ወንድሙ ንጉሴ በ12 ዓመት ጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጣ ተወሰነ።

ቅጣቱን የወሰነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው።

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ተደራራቢ ክሶችን አቅርቦ ነበር።

ተከሳሹ የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ ደንበኛ ከሆነው የቢፍቱ ስላሴ ህብረት ስራ ማህበር ሒሳብ ቁጥር ተመሳስሎ በተዘጋጀ ሀሰተኛ ቼክ እና በድርጅቱ የቼክ ፈራሚ 3 ግለሰቦች ተመሳስሎ በተፈረመ ቼክ ለአሰፋ ሰልቤና 200 ሺህ ብር እንዲከፈል የታዘዘ በማስመሰል ቼኩን ለባንክ ማቅረቡ ተጠቅሷል።

በመስከረም 23 ቀን 2013 ዓ.ም ደግሞ ኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ ጀሞ ቅርንጫፍ በተመሳሳይ ስምና ፊርማ የ430 ሺህ ብር ሀሰተኛ ቼክ ይዞ በመቅረብ በሀሰተኛ ማንነት አሰፋ ሰልቤና ነኝ በማለት ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ እና አሰፋ ሰልቤና ተብሎ ሀሰተኛ ስም በተከፈተ ሒሳብ ገቢ ካደረገ በኋላ በተለያዩ ቀናቶች ክፍያ እንዲፈፀምለት ማድረጉም ተዘርዝሯል።

ተከሳሹ በጥር 2 ቀን 2012 ዓ.ም ጌትነትና አስተዋይ የኮንስትራክሽን ስራ ህብረት ስራ ማህበር ሒሳብ ከሆነው ሕጋዊ ፈራሚው ጌትነት ፀጋዬ የተባለ ግለሰብ ሳይፈርምና ክፍያ ሳያዝበት ለደቻሳ ገመዳ 250 ሺህ ብር የታዘዘ በማስመሰል የገንዘብ መጠን የተጻፈበትና የተፈረመበትን ሃሰተኛ ቼክ በንግድ ባንክ ፑሽኪን አደባባይ ቅርንጫፍ ይዞ በመቅረብና የራሱን ማንነት በመደበቅ ደቻሳ ገመዳ ነኝ በማለት መታወቂያ በመያዝ የ250 ሺህ ብር ክፍያ እንዲፈፀምለት ማድረጉም በክሱ ተመላክቷል።

ተከሳሹ በተጨማሪም የንግድ ባንክ ደንበኛ ከሆኑት ዘ-ሀንገር ፕሮጀክት ኢትዮጵያ የሒሳብ ቁጥር ባንኩ ከሚሰጠው ቼክ ጋር ተመሳስሎ በተዘጋጀ ሀሰተኛ ቼክ ላይ የድርጅቱን የቼክ ፈራሚዎችን ፊርማ ተመሳስሎ በተፈረመ ለኤፍሬም አዲሱ 200 ሺህ ብር እንዲከፈል የታዘዘ በማስመሰል ማንነቱን በመደበቅ ኤፍሬም አዲሱ ነኝ ብሎ ሀሰተኛ መታወቂያ በመያዝ ንግድ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ በመቅረብ 200 ሺህ ብር




ክፍያ እንዲፈፀምለት ማድረጉም ተጠቅሶ በቀረበበት ሌላኛው ክስ ላይ ሰፍሯል።

በዚህ መልኩ ተከሳሹ ማንነቱን በመደበቅ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን ለክፍያ በማቅረብ በለተያዩ ባንኮች ላይ በከባድ አታላይነት ወንጀል በመፈጸም ከ4 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ጉዳት ማድረሱ ተጠቅሷል።

ተከሳሹ የቀረበበት የወንጀል ድርጊትን በሚመለከት ዐቃቤ ሕግ የተለያዩ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረቡን ፋና ዘግቧል።

ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን መርምሮ ተከሳሹ በተከሰሰበት ተደራራቢ ድንጋጌዎች እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል።

ተከሳሹ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን መከላከል ባለመቻሉ ሀሰተኛ የህዝባዊ ሰነዶችን በመገልገል እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ከባድ አታላይነት ወንጀል እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል።

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየቶችን በመያዝ መርምሮ ዛሬ በዋለው ችሎት ተከሳሹን በ12 አመት ጽኑ እስራትና በ10 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል።

# ከ82 ሚሊየን ብር በላይ ግብርና ታክስ በማሳጣት በመንግስት ላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ተከሳሽ ጥፋተኛ ተባለ

ከ82 ሚሊየን ብር በላይ ግብርና ታክስ በማሳጣት በመንግስት ላይ ጉዳት አድርሷል የተባለው ተከሳሽ ጥፋተኛ ተባለ።

የጥፋተኝነት ፍርዱን የሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው።

ተከሳሹ ሰለሞን ገ/እግዛብሔር አፅብሃ ሲሆን፥ የፍትህ ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ተደራራቢ ክሶችን አቅርቦበታል።

ተከሳሹ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ነሃሴ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ እንደተሰጠ የሚገልጽ ቢኒያም አድማሱ በሚል አየለች ሙሉነህ አበራ ለተባለች ግለሰብ የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመጠቀም የተጨማሪ እሴት ታክስ እጅ በእጅ ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ በመውሰድ ከጁፒተር ንግድ ስራ ኃ/የተ የግ/ማህበር ጋር እና ከሀሮን ኮምፒዩተር ስራ ኃ/የተ የግ/ማህበር ጋር በመዋዋል የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በመውሰድ በሌላ ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መጠቀሙ በክሱ ተዘርዝሯል።

በሌላ ክስም ተከሳሹ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በግብር ከፋይነት በተመዘገበች ግለሰብ ስም ነሐሴ 22 ቀን 2011 ዓ.ም ከፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ እንደተሰጠ የሚገልጽ መታወቂያ በመጠቀም የንግድ ስራ በመስራት 77 ሚሊየን 232 ሺህ 275 ብር ከ98 ሳንቲም ግብርና ታክስ እንዲጭበረበር በማድረግ እንዲሁም በሌላ ሰው ስም ንግድ ስራ መስራት ወንጀል ክስ ቀርቦበታል።

በተጨማሪም ተከሳሹ በግብር ከፋይ መለያ የተመዘገበች አመለ አድማሱ በተባለች ግለሰብ ስም ደግሞ ህዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ እንደተሰጠ የሚገልጽ ሀሰተኛ የውክልና ማስረጃ በመጠቀም እንዲሁም ቢኒያም አድማሱ ቦጋለ በሚል ሀሰተኛ ማንነት ተጠቅሞ ባወጣው ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ በመጠቀም የንግድ ስራ በመስራት 4 ሚሊየን 993 ሺህ 761 ብር ከ36 ሳንቲም እንዲጭበረበር በማድረግ በሌላ ሰው ስም የንግድ ስራ መስራት ወንጀል መከሰሱም በዝርዝር ቀርቧል።

በተጨማሪም ተከሳሹ የንግድ ስራ አዋጅ ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ከቦሌ ክፍለ




ከተማ ወረዳ 3 ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ ጽ/ቤት እንደተሰጠ የሚገልጽ ሀሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ በመያዝ ተከሳሹ ጥር 25 ቀን 2012 ዓ.ም ከሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ኤጀንሲ ተረጋግጦ እንደተሰጠ የሚገልጽ ከሰለሞን ገ/እግዛብሔር ለቢኒያም አድማሱ የሚል ሀሰተኛ የውክልና ማስረጃን መገልገሉ ተጠቅሷል፡፡

በዚሁ ሀሰተኛ ማስረጃ በስሙ ከየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ንግድ ጽ/ቤት ቢሮ የችርቻሮ ንግድ ፈቃድ እና የኮንስትራክሽን ንግድ ፈቃድ በማውጣት ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም በሀሰተኛ ሰነድ የንግድ ፈቃድ ማውጣቱ ተጠቁሟል፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሹ የቀረበበትን ተደራራቢ ክስ በሚመለከት ዐቃቤ ሕግ ከስምንት በላይ የሰው ምስክሮችን እና የተያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦበታል።

ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን መርምሮ ተከሳሹ እንዲከላከል በሰጠው ብይን መሰረት በተገቢ መልኩ መከላከል አለመቻሉ ተጠቅሶ በዛሬው ቀጠሮ መሰጠቱን ፋና ዘግቧል።

በዚህም መሰረት ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎበታል።

የሃይማኖት ተቋማት ሙስናን የሚፀየፍ እና መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ለማፍራት ሚናቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ተጠየቀ

የኃይማኖት ተቋማት ሙስናን የሚፀየፍ እና በመልካም ሥነምግባር የታነፀ ዜጋን ለማፍራት በሚደረገው ጥረት ሚናቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጠየቀ።